# የይቅርታ ሕጎችና አፈጻጸማቸው በባሕር ዳር ማረሚያ ቤት

*በላይነህ አድማሱ እጅጉ*[§]
*ዓለሙ ዳኛው ፈለቀ*[a]

## አህጽሮት

*ይቅርታ ወንጀልን ፈጽመው ጥፋተኛ በተባሉ ወንጀለኞች ላይ የተወሰነው የወንጀል ቅጣት በአስፈጻሚው የመንግስት አካል አማካኝነት የሚቀነስበት ወይም የሚሻሻልበት ሥርዓት ነው። መንግስት ወንጀለኞች የሚያሳዩትን የባህሪ መሻሻልና በጥፋታቸው መጸጸት መነሻ በማድረግ ከተወሰነባቸው ቅጣት ውስጥ ከፊሉ ቀሪ እንዲሆንላቸው በማድረግ የይቅርታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል። ይህም በብዙ አግሮች የተለመደና አሰራሩም በህግ የሚመራ ነው። በዚህ ጥናት ውስጥ የይቅርታ አሰጣጥ ሥርዓትን በህግ እንዲመራ በማድረግ ይቅርታ የሚሰጡ የጥቂት አገሮች ተሞክሮ ተዳስሷል። ኢትዮጵያም ይቅርታን በፌዴራልና በክልል የህግ ማእቀፎች እንዲካተት በማድረግ ለታራሚዎች በየጊዜው ይቅርታን ታደርጋለች።*

*የዚህ ጥናት አላማ የባሕር ዳር ማረሚያቤት የይቅርታ አሰጣጥ ሥርዓት ከኢፌዴሪና ከአማራ ክልል ሕግጋት አንጻር ምን እንደሚመስል መመርመር ነው። የጥናት ዘዴው አይነታዊ ሲሆን በባሕር ዳር ማረሚያቤት በይቅርታ አሰጣጥ ሂደት የሚስተዋሉትን የሕግና የአፈጻጸም ችግሮች ለይቶ የመፍትሄ ሃሳቦችን በጥናቱ ለማመልከት ጥረት ተደርጓል።*

*በጥናቱም በአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅና መመሪያ ውስጥ የሰፈሩ የይቅርታ ቅድመሁኔታዎች ግልጽነት የጎደላቸውና ለአፈጻጸም አስቸጋሪ መሆናቸው ከመረጋገጡም በላይ በነዚህ የክልል ሕግጋትና በፌዴራል ሕጎች መካከል የሚስተዋሉት መጣረስና ልዩነት ተለይተው የመፍትሄ ሃሳቦች ተጠቁመዋል።*

**ቁልፍ ቃላት-** ይቅርታ፤ የይቅርታ ተጠቃሚ፣ የይቅርታ አሰጣጥ ሥርዓት፣ የወንጀል ቅጣት

## መግቢያ

ይቅርታ በፍርድ ጥፋተኛ ተብለው በማረሚያቤት የተወሰነ ቅጣታቸውን ተግባራዊ እያደረጉ እያለ፣ ታራሚዎች በጥፋታቸው ተጸጽተው የይቅርታ ማመልከቻ ለሚመለከተው አካል ሲያቀርቡ ወይም በሌላ በሚመለከተው የመንግሥት አካል የይቅርታ ጥያቄ ሲቀርብ ታራሚዎች የሚገኙበትን ሁኔታ፣ ማረሚያቤት አስፈላጊውን ጥናት በማድረግና የታራሚዎችን ባሕርይ በመገምገም ቅጣቱ ከመጠናቀቁ በፊት በሁኔታ ወይም ያለሁኔታ እንዲለቀቁ የሚደረጉበት ሥርዓት

---

[§] በሕግ የመጀመሪያ ድግሪ (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)፣ ሁለተኛ ዲግሪ በወንጀል ሕግ (አምስተርዳም ዩኒቨርሲቲ)፣ በሕግ ረዳት ፕሮፌሰር፣

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት፡ badmaasu7@gmail.com ወይም belaynehv@yahoo.com

[a] በሕግ የመጀመሪያ ድግሪ ( ጅማ ዩኒቨርሲቲ )፣ ሁለተኛ ዲግሪ በወንጀል ሕግ እና ሰብአዊ መብት (ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ)፣ ሌክቸረር፣

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት፡ alemudag@gmail.com

ነው፡፡ [1] ይህ ሥርዓት እንደሌሎች አገሮች ሁሉ በኢትዮጵያም የወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ አካል ሆኖ በሕግ እውቅናን ከማግኘቱም በላይ በፌዴራልና በክልል መንግስታት ስር በተዋቀሩ ማረሚያቤቶችና የይቅርታ ቦርዶች አማካኝነት ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛል፡፡ ሆኖም በይቅርታ አሰጣጥ ሂደቱ የሚከናወኑ ተግባራት ከሕግና ከአፈጻጸም ችግሮች የጸዱ አይደሉም፡፡ በተለይ በአማራ ብሄራዊ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ማረሚያቤቶች አንዱ በሆነው ባሕር ዳር ማረሚያቤት በይቅርታ አሰጣጥ ረገድ ከሚስተዋሉ የሕግና የአተገባበር ችግሮች መካከል የይቅርታ ጥያቄ አቀራረቡ ግልጽነት የጎደለው መሆኑ፣ የይቅርታ ተጠቃሚዎችን በተመለከተ የባሕርይ መመዘኛ መስፈርት አለመኖሩ፣ የእርቅ አፈጻጸሙ ሂደት የረዘመና ባለቤት የሌለው መሆኑና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡ እነዚህን ችግሮች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በማጥናት ዘላቂ የሆነ መፍትሄ በማፈላለግ ለሕግና ለፖሊሲ አውጭዎች እንዲሁም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ለመጠቀም በማሰብ ይህ ጥናት ተከናውኗል፡፡

የጥናቱም መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1. የይቅርታ ቅድመሁኔታዎች ግልጽና የተሟሉ ናቸውን?
2. እነዚህ ቅድመሁኔታዎች ላፈጻጸም ምቹ ናቸውን?
3. የይቅርታ ተጠቃሚ ታራሚዎች እነማን ናቸዉ?
4. ታራሚዎች ከወንጀል ሰለባዎች ወይም ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲፈጽሙ የሚጠበቀው እርቅ ለይቅርታ መስጠት አስገዳጅ ነውን? ታራሚዎች እርቁን እንዴት ሊፈጽሙ ይችላሉ? እርቁ ለመፈጸሙ ማቅረብ ያለባቸው ማስረጃ ምንድን ነው?

የነዚህ ጥያቄዎች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መመለስ ታራሚዎች የይቅርታ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያጋጥሟቸውን የሕግና የአፈጻጸም ችግሮች በጥናት በመለየት የመፍትሄ ሃሳቦችን አመንጭቶ ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም ለፖሊሲና ለሕግ አውጭዎች ለመጠቆም ያስችላል፡፡ የጥናቱ ዘዴ አይነታዊ ሲሆን፣ መረጃዎችም በቃለመጠይቅ፣ በቡድንተኮር ውይይት (Focus group discussion)፣ በምልከታና አግባብነት ባላቸው ሰነዶች ተሰብስበዋል፡፡

በዚህ መሠረት በፌዴራል መንግስቱና በአማራ ብሄራዊ ክልል መንግሥት የይቅርታ ሕጎች እንዲሁም በአማራ ክልል ከሚገኙ ማረሚያቤቶች አንዱ በሆነው ባሕር ዳር ማረሚያቤት በይቅርታ አሰጣጥ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በሳይንሳዊ ዘዴ በማጥናት የመፍትሄ ሃሳቦችን በጥናቱ ለማመልከት ተሞክሯል፡፡

## 1. የይቅርታ ምንነትና ጽንሰ-ሃሳብ

ይቅርታ በእለት ተእለት የሰው ልጆች መስተጋብር ውስጥ ይስተዋላል፡፡ የሰው ልጅ በደል ወይም ስህተት ሲፈጸምበት በድርጊቱ ተበሳጭቶ ለበቀል ወይም ለወቀሳ የሚነሳሳውን ያህል ለይቅርታም ያንኑ ያህል ቦታ ይሰጣል፡፡[2] ከባህል ባህል ወይም

---

[1] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ፣አዋጅ ቁጥር 414/1997፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣1997፣ አንቀፅ 229 (ከዚህ በኋላ የኢፌዴሪ የወንጀልህግ)፡፡

[2] Nicola Lacey and Hanna Pickard, 'To Blame or to Forgive? Reconciling Punishment and Forgiveness in Criminal Justice', *Oxford Journal of Legal Studies*, (2015) pp. 1-32, p. 1, available at http://eprints.lse.ac.uk/60379 last accessed on May 20, 2017.

ከአገር አገር ደረጃውና ይቅር የሚባባሉበት መንገድ ይለያይ እንጂ በደል ወይም ስህተት ሲፈጸም በድርጊቱ ተጸጽቶ 'ይቅርታ አድርግልኝ ወይም ማረኝ' መባባሉ የሰው ልጆች የዘወትር ትዕይንት ነው፡፡[3] ይህም ሀይማኖታዊ መነሻ ያለው ሲሆን ሰዎች ሀጢያት ወይም በደል በመፈጸማቸው ተጸጽተው ፈጣሪያቸው ይቅርታ ወይም ምህረት እንዲያደርግላቸው የሚማጸኑበት ወይም ንስሀ የሚገቡበት መንገድ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህም ከበደላቸው ወይም ከመጥፎ ተግባራቸው በመነሳት ተጸጽተው ያለፈ በደላቸው ይደመሰስላቸው ዘንድ ከፈጣሪያቸው ጋር የሚገናኙበት እድል ከመሆኑም በላይ በደል ወይም ሀጢያት ድጋሜ ላይሰሩ ንስሃ የሚገቡበት ሥርዓት ሆኖ ያገለግላል፡፡[4] ከላይ የተነሳውን የሰው ልጆች በእለት ተእለት መስተጋብራቸው በሚፈጥሩት በደል ወይም ስህተት የሚያቀርቡትን ይቅርታ ለአንባቢያን በመተው በዚህ ጥናት በወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት ለተጣለባቸው ሰዎች በመንግሥት በኩል የሚደረገው ይቅርታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

እንዲህ አይነቱ የይቅርታ አሰጣጥ እንዴት እንደሚፈጸም ከማየት በፊት የቃሉን ፍቺ ማብራራት በጽንሰሃሳቡ ላይ ያለውን ግንዛቤ ለማስረዳት ስለሚጠቅም ይቅርታ ምን ማለት እንደሆነ የተለያዩ ጸሐፍት ስራዎች ተቃኝተዋል፡፡ ይቅርታ የሚለው የአማርኛ ቃል (pardon) ከሚለው እንግሊዝኛ ቃል ጋር አቻ መሆኑን በመገንዘብ በተለያዩ ጸሕፍቶች የተጻፉ የእንግሊዝኛ ድርሳናትን በማንበብ የይቅርታን ጽንሰሃሳብ ይበልጥ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይቅርታ በጥንታዊ የፈረንሳይ ሕግ ውስጥ ተካትቶ የሚገኝ ሲሆን ቃሉም ከላቲን ቃል *(perdonare)* [5]የተወሰደና ወደአማርኛ ሲመለስ መስጠት (መፍቀድ) ማለት ሲሆን፣ የወንጀል ጥፋት ላጠፉ ሰዎች በመንግሰት የሚፈቀድ ስጦታ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡[6] በወንጀል ፍትህ አስተዳደር አዘውትሮ ተግባራዊ የሚደረገው ይቅርታ ከሁለት የእንግሊዝኛ ቃላት 'par´ እና ´don' ከሚሉት የተወሰደና ሁለት ጽንሰሃሳቦችን የያዘ እንደሆነ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡ ይኸውም par ማለት መተው፣ መርሳት ወይም ነገሩን እንዳልተፈጠረ አድርጎ መገንዘብን ሲያመላክት don ደግሞ ስጦታን፣ ችሮታን፣ ልገሳን ይወክላል፡፡ ስለዚህ የሁለቱ ቃላት ጥምር ፍቺ ይቅርታ ለተፈጸመ አንድ በደል ወይም ጥፋት ምህረት ወይም ይቅርታ ማድረግን ያመለክታል፡፡[7]

ይቅርታ ማለት በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውስጥ ወንጀል የሰራን ግለሰብ ቅጣቱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዳይፈጸምበት የሚሰጥ ይቅር ማለት ወይም መተውን[8] የሚመለከት ጽንሰሃሳብ እንደሆነ ብላክስ ሎው (የሕግ መዝገበቃላት) ይገልጻል፡፡ የይቅርታ ትርጉም በሌሎች መዝገበቃላትም ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ተገልጾ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ የዌብስተር መዝገበቃላት ይቅርታ ለሚለው ቃል የሰጠው

---

[3] ዝኒ ከማሁ፡፡

[4] Julian H. Wright, Jr, 'Pardon in the Hebrew Bible and Modern Law', *Regent University Law Review*, vol. 3, No. 1, (1993) p. 6

[5] Amnesty and pardon, Encyclopedia of crime and Justice, 2002, retrieved from http://www.encyclopedia.com last accessed on 15 Agust 2017.

[6] ዝኒ ከማሁ፡፡

[7] Pardon and Amnesty, the criminal Magazine, No 2, 1985.

[8] Black's Law Dictionary, 9th ed., s.v. "pardon".

ፍቺ አንድ ሰው በፈጸመው የወንጀል ድርጊት ተከሶ በፍርድቤት የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ ከተላለፈበት በኋላ ቅጣቱ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ እንዳይፈጸምበት የሚደረግበት አሰራር ወይም አግባብ እንደሆነ ያሳያል፡፡[9] ስታንሌይ ግሩፕ የተባለ ጸሃፊም እንዲሁ ይቅርታ ማንኛውንም የወንጀል ውጤት ሙሉ በሙሉ ቀሪ የሚያደርግ ጽንሰሃሳብ ተደርጎ እንደሚወሰድ ይገልጻል፡፡[10]

ይህንኑ ቃል በጽንሰሃሳብ ደረጃ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ የመስኩ ባለሙያዎች ይተነትኑታል፡፡ ሱዛን ማርቲን የተባለች የዘርፉ ሊቅ ይቅርታ የሚለው ቃል ጠቅለል ያለና አስፈጻሚው የመንግሥት አካል በፍርድ ጥፋተኛ የተባሉ ወንጀለኞችን ከእስር ለመልቀቅ ወይም የተወሰነባቸውን የእስራት ቅጣት ለማቅለል የሚያልፍባቸውን ልዩ ልዩ የሕግ ስነሥርዓቶች አካትቶ የያዘ የቅጣት መቀነሻ ወይም ማቅለያ መንገድ እንደሆነ በመግለጽ ጽንሰሃሳቡን ታብራራለች፡፡[11] ማርሻልና ሆልምስ የተባሉ አሜሪካዊ ዳኞችም እንደዚሁ በ1833 [12] እና 1927 [13] እንደቅደምተከተላቸው ይቅርታን ከፍ ብሎ ከተሰጠው ማብራሪያ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ገልጸውታል፡፡

ከላይ በባለሙያዎች የተገለጸው የይቅርታ ጽንሰሃሳብ ከወንጀል ፍትህ አስተዳደር ጋር ተያያዥነት ያለውና በፍርድ ጥፋተኛ የተባለ ወንጀለኛ በመንግሥት ይቅር የሚባልበትን ሥርዓት ያሳየ እንደሆነ በግልጽ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ጽንሰሃሳቡን ይበልጥ ለመገንዘብም ከይቅርታ ጋር ቁርኝት ያላቸውን መሰረታዊ ነጥቦች መመልከቱ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውስጥ የሚታወቀው ይቅርታ በማህበራዊ ወይም በኃይማኖታዊ ኑሮ በማንኛውም ግለሰብ ከሚሰጥ ይቅርታ የተለየ የሚያደርገው የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት ባለቤት በሆነው መንግሥት ከፍተኛ ባለስልጣን የሚሰጥ መሆኑ ነው፡፡[14] በዚህ ጽንሰሃሳብ መነሻነት በብዙ አገሮች ይቅርታ በአስፈጻሚው የመንግሥት አካል ይታወጃል፡፡[15] ይህም ወንጀል ፈጽመው በፍርድ ጥፋተኛ ለተባሉት ወንጀለኞች ህዝብና መንግሥት ይቅርታን የሚሰጡበት ሥርዓት በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውስጥ የሚታወቀው ይቅርታ የሚይዘው አንዱ ባሕርይ ነው፡፡

የይቅርታ ይዘት የሚያካትተው ሌላ ነጥብ ይቅርታ የሚሰጠው በፍርድ ወንጀለኛ መሆናቸው ለተወሰነባቸው ሰዎች መሆኑ ነው፡፡ ይቅርታ ለማንኛውም ሰው

---

[9] www.merriam-webster.com/dictionary/pardon last accessed on 15 Agust 2017.

[10] Stanley Grupp, Some Historical Aspects of the Pardon in England,, the American Journal of Legal History, Vol. 7, No. 1( Jan. , 1963), p. 51.

[11] Susan E. Martin, 1983, 'Commutation of Prison Sentences: Practice, Promise, and Limitation', 29 CRimE & DELINQ. 593, 593

[12] United States v. Wilson 32 U.S. 150 (1833).

[13] *Biddle v. Perovich*, 274 U.S. 480, 486 (1927).

[14] Ekta Bharati & Niharika Sala, President's Power to Pardon, *Journal On Contemporary Issues of Law (JCIL)* Vol. 2 Issue 2, p. 1.

[15] Nada Simjanoska, Meaning of the Terms Amnesty and Pardon in the Macedonian Criminal Law, *(JPMNT) Journal of Process Management – New Technologies, International,* Vol. 5, No 1, (2017), p. 17; Henry Weihofen, Consolidation of Pardon and Parole: A Wrong Approach, *Journal of Criminal Law and Criminology* (1931-1951),Vol. 30, No. 4 , (1939), p. 537.

የሚሰጥ ሳይሆን በፍርድቤት ጥፋተኛ መሆናቸው ተወስኖ በማረሚያቤት ቆይታቸው በጥፋታቸው መጸጸታቸውንና በባሕርይ መሻሻል ላሳዩ ሰዎች ነው፡፡ [16] የይቅርታ ተጠቃሚ የሆነው ሰው ከወንጀል ክስ ወይም ቅጣት ነጻ እንዲሆን መደረጉ የይቅርታ ውጤትና መገለጫ እንደሆነ ይታመናል፡፡ [17] በዚህ መሠረት ይቅርታ የተደረገለት ወንጀለኛ ከእስር ተለቅቆ፣ በፍርድ የተደረገበት የመብት ክልከላ ተነስቶለት ነጻ ሆኖ የመንቀሳቀስ እድል ያገኛል፡፡ በመጨረሻም ይቅርታ የተደረገለት ሰው ቅጣቱ እንደሚሰረዝለትና ቀደም ሲል የተላለፈበት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተነስቶለት ከዚህ በፊት ወንጀል እንዳልፈጸመ ንጹህ ሰው ተቆጥሮ በማንኛውም እንቅስቃሴ ሊሳተፍ እንደሚችል ጸሐፍት ይሟገታሉ፡፡ [18] ይህንን ሐሳብ የሚያጠናክሩ ፍርዶችም በአንዳንድ የአሜሪካ ዳኞች ተሰጥተዋል፡፡ እነዚህ ፍርዶችም በፍትህ ስርአቱ ውስጥ የይቅርታ ውጤትን አስመልክቶ የክርክር መነሻ ሐሳብ ሆነው ሲያገለግሉ ይስተዋላል፡፡[19]

ከላይ የተበራራው የይቅርታ ጽንሰሃሳብ በኢትዮጵያ የሕግ ማዕቀፍም የራሱን ሥፍራ ይዞ ይገኛል፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በወጡ ህገመንግስታትና [20] የወንጀል ሕጎች [21] ይቅርታን አስመልክቶ የየራሳቸውን ድንጋጌ የያዙ ቢሆኑም የይቅርታን ምንነት ወይም ትርጓሜ ትኩረት አልሰጡትም፡፡ በኢፌዴሪ ህገመንግሰትና የወንጀል

---

[16] ዝኒ ከማሁ, *ገፅ* 17::

[17] ዝኒ ከማሁ፡፡

[18] Henry Weihofen, The Effect of a Pardon, *University of Pennsylvania Law Review and American Law Register,* Vol. 88, No. 2 (Dec., 1939), p. 177.

[19] 7I U. S. 333, 380 (i866), Illinois Central Ry. v. Bosworth, I33 U. S. 92, I03 (I889) ; Ex parte Hunt, IO Ark. 284, 288 (I850); People v. Hale, 64 Cal. App. 523, 533, 222 Pac. I48, I52 (I923); In re Emmons, 29 Cal. App. I2I, I23, I54 Pac. 6I9, 620 (19I5); In the Matter of Executive Communication, I4 Fla. 3I8, 319 (I872) ; Dade Coal Co. v. Haslett, 83 Ga. 549, 55I, io S. E. 435 (I889); United States v. Athens Armory, 35 Ga. 344, 363 (i868); Kelley v. State, 204 Ind. 6i2, 625, i85 N. E. 453, 458 (i933); Cowan v. Prowse, 93 Ky. I56, I72, I9 S. W. 407, 4II (i892); State v. Baptiste and Martini, 26 La. Ann. i34, I37 (i874); Penobscot Bar v. Kimball, 64 Me. I40, I46 (I875); Jones v. Board of Registrars, 56 Miss. 766, 768 (I879); People v. Court of Sessions, 14I N. Y. 288, 294, 36 N. E. 386, 388 (i894); State v. Keith, 63 N. C. I40, I43 (i868); Knapp v. Thomas, 39 Ohio St. 377, 381 (i883); Wood v. Fitzgerald, 3 Ore. 568, 577 (I870); Diehl v. Rodgers, I69 Pa. 3I6, 322, 32 Atl. 424, 426 (I895) ; Carr v. State, i9 Tex. App. 635, 66i (i885); In re Conditional Discharge of Convicts, 73 Vt. 414, 428, 5I Atl. io, 14 (I90I); Edwards v. Commonwealth, 78 Va. 39, 43 (1883). As cited in Henry Weihofen, ' The Effect of a Pardon', *University of Pennsylvania Law Review and American Law Register*, Vol. 88, No. 2 (Dec., 1939), p. 177.

[20] Ethiopian Constitution of 1931, Established in the reign of His Majesty Hail`e Sellassi´e I, 16th July 1931, Article 16, Proclamation Promulgating the Revised Constitution of the Empire of Ethiopia Conquering Lion of the Tribe of Judah Haile Selassie I Elect of God, Emperor of Ethiopia, (1955), Article 35, The constitution of the Peoples of Democratic Republic of Ethiopia, proclamation No. 1of 1987, *Negarit Gazetta*, , No.1, Addis Ababa, Article 86(2)(d), The Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, Proclamation No 1 /1995 , *Federal Negarit* Gazeta, (1995)1, Article 71 (7).

[21] የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣(1949)፣ አንቀጽ 239 ( ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ)፤ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 1፣አንቀጽ 229፡፡

ሕግ የተደነገገውን ይቅርታ ለማስፈጸም ያግዝ ዘንድ የኢፌዴሪ መንግሥትና የክልል መንግስታት የየራሳቸውን የማስፈጸሚያ አዋጆችና መመሪያዎች አውጥተው በስራ ላይ ያዋሉ ሲሆን እነዚህ ሕግጋት ይቅርታን የተመለከቱ ዝርዝር አሰራሮችን ከመደንገጋቸው በተጨማሪ ቃሉን ከፍ ብሎ በተገለጸው መንገድ ተርጉመውታል፡፡ የየክልሎች አዋጆችና [22] መመሪያዎች ሲመረመሩ ይቅርታን ከመተርጎም አንጻር ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው በመሆናቸው ለዚህ ጥናት አላማ የኢፌዴሪንና የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥትን የይቅርታ አዋጆችንና መመሪያዎችን ብቻ መመልከቱ በተመራማሪዎቹ እምነት በቂ ሆኖ ተግኝቷል፡፡ በመሆኑም ሕግጋቱ ይቅርታን የተረጎሙበት አግባብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የኢፌዴሪ የይቅርታ አዋጅ ቁጥረ 840/2006 ይቅርታን እንደሚከተለው ተርጉሞታል፡፡ "ይቅርታ ማለት የቅጣት ፍርድ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ወይም የቅጣት ፍርዱ አፈፃፀምና ዓይነት ቀለል ተደርጎ እንዲፈፀም ማድረግ ነው"፡፡ [23] የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የይቅርታ አዋጅ ለቃሉ ቀጥተኛ ትርጉም ባይሰጥም የይቅርታ ጥያቄን ትርጉም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የይቅርታ አዋጅ ለይቅርታ ከተሰጠው ትርጉም ጋር ተቀራራቢ በሆነ መልኩ ተርጉሞታል፡፡[24] ይሁን እንጂ በአዋጁ የተመለከተውን ክፍተት ለማሟላት በሚመስል መልኩ የአ.ብ.ክ.መ የተሻሻለው የይቅርታ አሰጣጥ መስፈርት መወሰኛ መመሪያ ለይቅርታ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የይቅርታ አዋጅ ለይቅርታ ከሰጠው ትርጉም ጋር አንድ ዓይነት ፍቺ አስፍሮ ይገኛል፡፡ ምክንያቱም ይህ መመሪያ የቅርታን፤ "ይቅርታ ማለት የቅጣት ፍርድ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ወይም የቅጣት ፍርዱ አፈፃፀምና ዓይነት ቀለል ተደርጎ እንዲፈፀም ማድረግ ነው"፡፡[25]

በኢትዮጵያ ህግጋት ለይቅርታ የተሰጠው ትርጓሜ ሲታይ የተለያዩ ጸሕፍት የይቅርታን ጽንሰሃሳብ ሲያብራሩ ከሰጧቸው ገለጻዎች ጋር በይዘት ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህም የየኢትዮጵያና የአብክመ የሕግ ማእቀፍ፣ ይቅርታ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት ያለውን ሚና በአግባቡ የሚያመላክት ነው፡፡ ሕግጋቱ ለይቅርታ ከሰጡት ትርጓሜ ታራሚዎች የተጣለባቸውን ቅጣት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ሳይፈጽሙ ከእስር እንዲለቀቁና የበደሉትን ማህበረሰብ እንዲክሱ የሚደረግበት ሥርዓት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

---

[22] የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ የይቅርታን አፈጻጸም ስነሥርዓት ለመወሰን የወጣ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 11/1998፣ መገለተ ኦሮሚያ፣ (ሐምሌ 5 1998)፣ የተሻሻ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግሥት የይቅርታ አሰጣጥ ሥነሥርዓት አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 157/2007፣ ደቡብ ነጋሪት ጋዜጣ፣ (የካቲት 2007 ዓ.ም) እና የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የይቅርታ አሰጣጥ ስነ ስርዒት ለመደንገግ የወጣ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 112/1998 ዒ/ም፣ የትግራይ ነጋሪት ጋዜጣ፣ (ሐምሌ 4 1998)፡፡

[23] የኢፌዴሪ የይቅርታ አሰጣጥና አፈፃፀም ሥነሥርዓትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 840/2006፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ (2006)፣አንቀጽ 2(1) (ከዚህ በኋላ የፌዴራል የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ ተብሎ ይነበባል፡፡)

[24] በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የይቅርታ አሰጣጥ ሥርዓት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር **136/1998**፣ዝክረሕግ፣ (1998)፣ቁጥር 21 (ከዚህ በኋላ የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ)፡፡ አንቀጽ 2(1) "*የይቅርታ ጥያቄ ማለት አንድ ፍርድ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ወይም የቅጣት አፈጻጸሙ ዓይነት በቀላል ሁኔታ እንዲፈጸም የሚቀርብ ጥያቄ ነው፡፡*"

[25] የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የይቅርታ አሰጣጥ መስፈርት መወሰኛ መመሪያ፣ መመሪያ ቁጥር 23/2007፣ የአማራ ብሄራዊ ክልል መስተዳደር ም/ቤት፣( ነሐሴ 29 ቀን 2009 ዓ.ም) ፣አንቀጽ 2(6) (ከዚህ በኋላ የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ መመሪያ)፣ አንቀጽ 2(6).

## 2. የይቅርታና የምህረት ተመሳስሎና ልዩነት

ይቅርታና ምህረት በጽንሰሃሳብ ደረጃ የተለያዩ ቢሆኑም በዘርፉ ባሉ ባለሙያዎችና ጉዳዩ በሚመለከታቸው ሌሎች ሰዎች መካከል ሁለቱን ጽንሰሃሳቦች አስመልክቶ የግንዛቤ ልዩነት አለ፡፡ በሌላ አገላለጽ በይቅርታና በምህረት መካከል ያለውን የጽንሰሃሳብ ልዩነት ባለመረዳት ሁለቱ አንድ እንደሆኑ በማሰብ አንዱ ሌላውን የተካ በሚመስል መልኩ ስራ ላይ ሲውሉ ይታያል፡፡[26] የዚህ ክፍል ዋና ዓላማም 'ይቅርታ' ከ'ምህረት' የሚለይባቸው ባሕርያት ምን እንደሆኑ በማሳየት በመካከላቸው ያለውን ብዥታ ለማጥራት ነው፡፡ ለዚህ ዓላማ መሳካትም የይቅርታ ትርጓሜና ጽንሰሃሳብ በቀደመው ክፍል እንደተብራራ ሁሉ ለንጽጽር ይመች ዘንድ 'ምህረት' የሚለውን ቃል ፍቺ ወይም ትርጉም መስጠቱ አስፈላጊ እንደሆነ በመረዳት እንደሚከተለው በአጭሩ ለማብራራት ጥረት ተደርጓል፡፡

ምህረት 'Amnesty' ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል አቻ ሲሆን የእንግሊዝኛው ቃል መነሻ 'አምነስቲያ' የሚለው የግሪክ ቃል እንደሆነ ይታወቃል፡፡[27] ትርጓሜውም በመንግሥት ላይ የተፈጸመ ወንጀልን ወይም ጥፋትን በመርሳት ወይም በማስተስረይ ወንጀሉ ወይም ጥፋቱ እንዳልነበረ በመቁጠር መንግሥት ወንጀለኞችን እንደንጹህ ሰው በመቁጠር ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው በሰላማዊ መንገድ እንዲኖሩ የሚያደርግበት ሥርዓት ነው፡፡[28] በዚህ አግባብ ለወንጀለኞች በመንግሥት የሚታወጀው ምህረት ከክስ ወይም ከፍርድ በፊት አሊያም ከፍርድ በኋላ ሊሆን ይችላል፡፡ ምህረት ለወንጀለኞች በመንግሥት የሚሰጥ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከይቅርታ ጋር የሚመሳሰልባቸው ባሕርያት አሉ፡፡ ይቅርታን ከምህረት ጋር የሚያመሳስለው አንዱና ዋናው ሁለቱም በመንግስት የሚሰጡ መሆናቸውና ቅጣትን ቀሪ ማድረግ መቻላቸው ነው፡፡ በምህረትም ይሁን በይቅርታ እንዲለቀቅ የሚደረግ ወንጀለኛ በፍርድ የተወሰነበት ቅጣት ሊቀርለትና ነጻ ሆኖ ሊንቀሳቀስ ይችላል፡፡ ይህም ይቅርታንና ምህረትን ሊያመሳስል የሚችል የሁለቱም ውጤት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

ይቅርታና ምህረት በዚህ መልኩ ይመሳሰሉ እንጂ በመካከላቸው ልዩነት የለም ማለት አይደለም፡፡ ሁለቱም በመንግሥት የሚሰጡና የወንጀለኛውን ቅጣት ቀሪ የሚያደርጉ ቢሆኑም የሚከተሉት ነጥቦች ይቅርታን ከምህረት ልዩ ያደርጉታል፡፡ ይቅርታ በአስፈጻሚው አካል የሚሰጥ ሲሆን ምህረት ብዙውን ጊዜ በሕግ አውጭው አካል ይታወጃል፡፡[29] ይህም ሁለቱን ጽንሰሃሳቦች ከተለያየ የመንግሥት አካል የሚመነጩና ተግባራዊ የሚደረጉ እንደሆኑ ያስገነዝባል፡፡ ይቅርታ ከምህረት የሚለይበት ሌላው ነጥብ ከወንጀሉ ዓይነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ምህረት በምንግስት ላይ በተፈጸሙ ፖለቲካነክ ወንጀሎች ለተጠረጠሩ፣ ለተከሰሱ ወይም ለተፈረደባቸው

---

[26] James F. Childress, The Amnesty Argument, *CrossCurrents*, Vol. 23, No. 3 , (1973), p. 311, available at http://www.jstor.org/stable/24457861 last accessed on 7 July 2017.

[27] Bouvier, "Definition of Amnesty", available at < http://dictionary.babylon.com/Amnesty last accessed July 25, 2017.

[28] *Black's Law Dictionary,* 9th ed., s.v. "Amnesty".

[29] Rene´Le´vy, Pardons and Amnesties as Policy Instruments in Contemporary France, *Crime and Justice*,Vol. 36, No. 1, (2007), p. 554, available at http://www.jstor.org last accessed on5 August 2017.

ወንጀለኞች የሚደረግ ሲሆን ይቅርታ ግን በማንኛውም ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው ለተፈረደባቸው ሰዎች ብቻ የሚሰጥ ነው፡፡ [30] በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ለማብራራት ሌላው ግምት ውስጥ መግባት ያለበት ነገር ይቅርታና ምህረት ሊያስገኙ የሚችሉት ውጤት ነው፡፡ ምህረት በፖለቲካ ነክ ወንጀሎች ለተጠረጠሩ፣ ለተከሰሱ ወይም ለተፈረደባቸው ሰዎች በሕግ አውጭው በኩል ሲታወጅ ምህረት የተደረገላቸው ወንጀለኞች ወንጀላቸው ሙሉ በሙሉ ተሰርዞ እንደንጹህ ዜጋ የመቆጠር መብትን ያጎናጽፋቸዋል፡፡ ምህረት የተደረገለት ሰው ምንም ዓይነት የቀደመ የወንጀል ጥፋተኝነት እንደሌለበት ተደርጎ በነጻነት በማንኛውም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የመሳተፍ እድል ይኖረዋል፡፡ [31] በተቃራኒው በይቅርታ የተለቀቀ ሰው የወንጀል ሪከርድ የሚኖርበትና ነጻነቱ በገደብ የተወሰነ ሊሆን ይችላል፡፡ [32] ገደቡን ተላልፎ የተገኘም እንደሆነ የተሰጠው ይቅርታ ተሰርዞ ወደነበረበት ማረሚያቤት ተመልሶ ቅጣቱን እንዲፈጽም ይደረጋል፡፡ ይህም በይቅርታ ከተለቀቀው ይልቅ በምህረት የተለቀቀው ሰው ሙሉ ነጻነት ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡

## 3. የይቅርታ አስፈላጊነት

ይቅርታ በማህበረሰባችን ውስጥ እንደመልካም እሴት ተደርጎ እንደሚወሰድና ይህም ከግለሰብ ግንኙነት አልፎ ወንጀል ፈጽመው በፍርድ ቅጣት ላረፈባቸው ግለሰቦችም እንደሚሰጥ በቀደሙት ርእሶቻችን ተመልክተናል፡፡ ይቅርታ በወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ ውስጥም የሚኖረው ሚና ከላይ ከተመለከትነው የተለየ አይደለም፡፡ ይቅርታ የህዝብና የመንግሥትን ጥቅም በመጻረር የወንጀል ሕግን ተላልፎ ወንጀልን ፈጽሞ የተገኘ ግለሰብ ከረጅም ጊዜ ምርመራና ማጣራት በኋላ ጥፋተኛ ለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ ቅጣት ካረፈበት በኋላ ቅጣቱ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ተሰርዞለት ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅሎ የበደለውን ግለሰብና ማህበረሰብ እንዲክስ የሚደረግበት ሥርዓት ነው፡፡ ይህ አሰራር በተለያዩ አገራት የወንጀል ፍትህ ሥርዓት ውስጥ ሕግን መሠረት አድርጎ ሲፈጸም ቆይቷል፤ እየተፈጸመም ነው፡፡

ወንጀለኛው የእንዲህ አይነቱ የይቅርታ ሥርዓት ተጠቃሚ የሚሆንባቸው ምክንያቶች በርካታ ናቸው፡፡ ዋና ዋናዎቹም ወንጀለኛው የባሕርይ መሻሻል አምጥቷል ተብሎ መታመኑ፣ በፍርድ የተላለፈበት ቅጣት የተጋነነ ነው ተብሎ መታሰቡ፣ በተፈጠረው የሕግ እና የፍሬ ነገር ስህተት ምክንያት ንጹሃን የቅጣት ሰለባ የመሆናቸው አጋጣሚና ጥፋተኞች በነገሥታት ወይም በርእሰ-ብሄሮች አማካኝነት ይቅርታ ሊደረግላቸው ይገባል ተብሎ መታመኑ ናቸው፡፡ [33] እነዚህ ምክንያቶች የይቅርታን አስፈላጊነት የሚያመላክቱ ስለሆኑ ከዚህ በታች ተራ በተራ ለመመልከት ይሞከራል፡፡

---

[30] ዝኒ ከማሁ፡፡

[31] Dejene Girma Janka, *A handbook on the criminal code of Ethiopia*, (2013), Addis Ababa, p. 200.

[32] ፀሐይ ወዳ፣ *የወንጀል ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች፣* (ጥር 19 ቀን 1994)፣ ገፅ 233፡፡

[33] Kathleen Dean Moore, *Pardons Justice, Mercy and the public Interest*, oxford University press, (1989), pp. 60-63::

በወንጀል ጥፋተኛ የተባለው ሰው በማረሚያቤት የተወሰነ ጊዜ ቆይታው የሚያሳየው የባሕርይ መሻሻል ለይቅርታ እንደዓቢይ ምክንያት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የፍርድ ቅጣቱ ላልተወሰነ ጊዜ (indeterminate sentencing) እንዲፈጸም የሚፈቅድ ሕግ ባላቸው አገሮች ለምሳሌ በአሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ አውስትራሊያና ሌሎችም[34] ታራሚው በፍርድቤት ከተላለፈው ቅጣት ከፊሉን በማረሚያቤት እንደቆየ የባሕርይ ማሻሻል ሊያሳይ ይችላል፡፡ ይህ የባሕርይ መሻሻል ከታየ በኋላ ታራሚውን በማረሚያቤት እንዲቆይ ማድረጉ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ታራሚው በአመክሮ ቦርድ አስተያየት ሰጭነት ከእስር እንዲለቀቅ ይደረጋል፡፡[35] የተወሰነ ጊዜ ቅጣት መርህን (determinate sentencing) በሚከተሉ አገሮች ደግሞ በፍርድቤት የተወሰነው የቅጣት ጊዜ ካላለቀ በቀር የታራሚውን ባሕርይ መሻሻል ግምት ውስጥ አስገብቶ ታራሚውን ከእስር ለመልቀቅ የሚያስችል አሰራር ባለመኖሩ ይቅርታን እንደአንድ አማራጭ አድርጎ የመገልገል ልምድ አለ፡፡[36] በሌላ አነጋገር ይቅርታ የባሕርይ መሻሻል ላሳዩ ታራሚዎች ሙሉ በሙሉ የእስራት ቅጣቱን ከመፈጸማቸው በፊት ከእስር እንዲለቀቁ ይደረጋል፡፡ይህም ታራሚዎች የባሕርይ መሻሻል ማሳየታቸው በማረሚያቤት የመቆየታቸውን ፋይዳ ዋጋ ያሳጣዋል፡፡[37]

ይቅርታን አስፈላጊ የሚያደርገው ሌላ ነጥብ የቅጣት መጋነን ነው፡፡[38] በመሠረቱ ቅጣት የሚጣልባቸው ምክንያቶች ወንጀለኛውን በመቅጣት እሱንና አጠቃላይ ማህበረሰቡን ማስተማር፣ ማስጠንቀቅና ወንጀለኛው ላጠፋው ጥፋት እንዲቀጣ ማድረግ ናቸው፡፡[39] ወንጀለኛውን ላጠፋው ጥፋት እንዲቀጣ የማድረጉ ነገር ወደበቀል እንዳያዘነብል አስፈላጊው ጥንቃቄ መወሰድ ያለበት ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ቅጣቱ ከጥፋቱ ያመዝንና ወይም ሳይመጣጠን ቀርቶ ወንጀለኛው ኢፍትሃዊ የሆነ ፍርድ ሊያጋጥመው ይችላል፡፡[40] እንዲህ አይነቱ የቅጣት መጋነንና የፍትህ መጓደል ሲያጋጥም አንዱ የማስተካከያ መንገድ የሚሆነው ፍርድ ቤቶች በሕግ የተሰጣቸውና የተለመደው ማስተካከያ መንገድ እንደይግባኝ፣ ሰበርና ፍርድን እንደገና ማየት የመሳሰሉ የውስጥ አሰራራቸው (self corrective devices) እንደሆነ ይታወቃል፡፡[41] በተፈጠረው የፍሬነገር፣ የስነሥርዓትና የመሰረታዊ ሕግ ስህተት ምክንያት በተጓደለው ፍትህ ቅር የተሰኘ ወገን በይግባኝ ወይም በአቤቱታ

---

[34] Fionadoherty, Indeterminate Sentencing Returns: The Invention of Supervised Release, *New York University Law Review*, Vol. 88:958, (June 2003), pp. 964-967.

[35] ዝኒ ከማሁ፡፡

[36] ዝኒ ከማሁ፡፡

[37] በላይነህና ሙሉነህ፣ የይቅርታ አፈጻጸም እና ውጤት በአማራ ክልል፣ *የአብክመ ፍትህ ቢሮ የህግ መጽሄት ሕግጋት*፣ ቅጽ 1፣ ቁጥር 3፣ (2004) ፣ ገጽ 102፡፡

[38] N. Trendle, Reviewing Miscarriages of Justice: The Pardon ational Society for the Reform of the Criminal Law, avai Papers/2004/Trendle Justice. pdf

[39] Mirko Bagaric, *Punishment and Sentencing: A Rational Approach*, Cavendish Publishing Limited, London, (2001), pp 33-50

[40] Kathleen Dean Moore, supra note 31, p. 131.

[41] Chad Flanders, Pardons and the Theory of the "Second Best", *Saint Louis University school of law, legal Studies* Research papers Serious No. 2013-11, pp. 1-4. ፍርድቤቶች የተሳሳተ ፍርድን ለማረም የሚጠቀሙባቸውን የውስጥ አሰራሮች በተመለከተ የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነሥርአት ሕግ ከአንቀጽ 180-189፣ የፌዴራል ፍርድቤቶች አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 25/1988፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ (1988)፣ አንቀጽ 10 እና የኢፌዴሪ የወንጀል ስነሥርአት ረቂቅ ህግ አንቀጽ 354 እንደቅደምተከተላቸው ይመልከቱ፡፡

እንዲስተካከልለት ጠይቆ ውጤት ሳያገኝ ቢቀርና በፍርድቤት የተጣለበትን የቅጣት ውሳኔ ለመፈጸም ወደ ማረሚያቤት ቢገባ ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት ማስተካከያ መንገዶች በተጨማሪ ለተፈጠረው የፍትህ መጓደል መፍትሄ ሆኖ የሚያገለግለው ይቅርታ መሆኑን ብዙ ጸሕፍት ያስረዳሉ፡፡[42] ፍርድ ቤቶች ጥፋተኛ በተባለ ግለሰብ ላይ ቅጣት ሲጥሉ ልዩ ልዩ የማቅለያና የማክበጃ ምክንያቶችን[43] ግምት ውስጥ በማስገባት ለጥፋቱ ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት እንደሚወስኑ የወንጀል ሕግ ፍልስፍና መርህ ቢሆንም በተግባር አልፎ አልፎም ቢሆን ከጥፋቱ ጋር የማይመጣጠን ቅጣት ሲወሰን ይስተዋላል፡፡ እንዲህ አይነቱ ቅጣት በወንጀል ሕግ የታለመውን ፍትህ ከማስፈን ይልቅ በጥፋተኛው ላይ የፍትህ መጓደልን ስለሚያስከትል በሕግ አግባብ ሊታረም ወይም ሊስተካከል እንደሚገባው ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም የፍትህ መጓደሉ ውሳኔውን በሰጠው ፍርድቤት ካልተስተካከለ በአስፈጻሚው አካል በሚሰጥ ይቅርታ የፍትህ መጓደሉ ሰለባ የሆነው ግለሰብ መፍትሄ ሊያገኝ እንደሚገባው የዘርፉ ጠበብት ይሞግታሉ፡፡[44]

ንጹሃን በተሳሳተ ፍርድ አማካኝነት ላልተገባ ቅጣት የመዳረጋቸው ጉዳይ ይቅርታን አስፈላጊ የሚያደርግ ሌላው ነጥብ እንደሆነ ባለሙያዎች ይስማማሉ፡፡[45] ሙር የተባለችው የዘርፉ ሊቅ የንጹሃንን ለተሳሳተ ፍርድ መጋለጥ ስታብራራ፣ ስህተት በየትኛውም ዘርፍ ወይም ሙያ ሊፈጠር እንደሚችልና ንጹሃን ተጎጅዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ የኒኩለር ቦንብንና የአውሮፕላን አደጋን በንጽጽር ትጠቅሳለች፡፡ በእነዚህ ዘርፎች የሚፈጠሩ ስህተቶች በሰው ልጆች ሕይወት ላይ ከፍተኛ አደጋን ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ሁሉ በፍርድ ሂደት የሚፈጠሩ ስህተቶችም በንጹሃን ላይ ከፍተኛ ፍትህ መጓደልና ልዩ ልዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች መጋለጥን ያስከትላሉ፡፡ ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት ከፍ ብሎ ለአብነት በተጠቀሱት የስራ ዘርፎች ለሚፈጠሩት አደጋዎች ፍቱን መፍትሄ (safety valves) የመኖራቸውን ያህል በፍትህ ዘርፉም በንጹሃን ላይ በተሳሳተ ፍርድ ምክንያት ለሚደርስባቸው ጉዳት መፍትሄ እንደሚያስፈልግ በማስረዳት ይቅርታ እንደመፍትሄ ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችል ሙር በመጽሐፏ ታብራራለች፡፡[46] ይህ ፍልስፍና በምእራባውያን ሀገሮች እውቅናን አግኝቶ በሕግ ማእቀፎቻቸው ተካትቶ እየተተገበረ እንደሚገኝ የታሪክ ድርሳናት ያሳያሉ፡፡ ለአብነትም ባረቦር የተባለው የሚሲሲፒ አገረገዥ ቁጥራቸው 200 የሚደርሱ ታራሚዎችን እ.አ.አ. በ2012 በይቅርታ የለቀቀበትና[47] አርባ ሁለተኛው የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ቢል ክሊንተን ባለቀ

[42] Margaret Colgate, Reinventing the President's Pardon Power, *American constitution Society for law and policy*, (October 2007), p. 10, retrieved from https://www.acslaw.org last accessed on 1 May 2017.

[43] Andrew Ashworth, *Mitigation and Aggravation at Sentencing,* Cambridge University Press (2011), P.21.

[44] James D. Barnett, 'The Grounds of Pardon, *Oregon Law Review,*, No. 6,(1927), pp 218 - 219 available at http://heinonline.org last accessed on 27 July 2017.

[45] Henry Weihofen, Pardon: An Extraordinary Remedy, *Rocky Mountain Law Review*, (1939-1940),, p.118 available at http://heinonline.org last accessed on 20 July 2017.

[46] Kathleen Dean Moore, supra note 33, p 131.

[47] P.S. Ruckman Jr , Barbour's last-minute rush to pardon, available at http://edition.cnn.com/2012/01/12/opinion/ruckman-haley-barbour-pardons/index.html last accessed 2 August 2017.

የስልጣን ዘመናቸው እ.አ.አ. በጥር 2001 ቁጥራቸው 140 ለሚደርሱ የአሜሪካ ፌደራል መንግሥት ታራሚዎች የሰጡት ይቅርታ ተጠቃሽ ነው፡፡[48] በጠቅላላው ይቅርታ በፍትህ ሥርዓት ውስጥ በሚፈጠሩ ስህተቶች ምክንያት ለፍትህ መጓደል ለተጋለጡ ንጹሃን ነጻ መውጣት ፍቱን መፍትሄ በመሆን ያገለግላል፡፡

በመጨረሻም ይቅርታ የሚሰጥበት ምክንያት የመንግሥት ወይም የንጉሣን ምህረትና ቸርነት እንደሆነ በዚህ ርዕስ መግቢያ ላይ ተመልክቷል፡፡ የብዙ ሀገራት መሪዎች ወይም ነገስታት በስልጣን ዘመናቸው ወንጀል ፈጽመው የተለያየ ቅጣት ተወስኖባቸው ፍርድ በመፈጸም ላይ ላሉ ታራሚዎች ይቅርታ ሲሰጡ መቆየታቸውን ጻሕፍት ያመላክታሉ፡፡[49] የሀገራት ነገሥታት በቀድሞው ጊዜ ለወንጀለኞች ይቅርታን ሲያደርጉ ወይም ምህረትን ሲያውጁ የታራሚውን ንጽህና ወይም የባሕርይ መሻሻል መሠረት ከማድረግ ይልቅ ያላቸውን የፖለቲካ፣ የሀብትና ማህበራዊ ደረጃ ልእልና መገለጫ አድርገው ነበር፡፡[50] በተለያዩ የአውሮፓ አገሮች በተለይም በእንግሊዝ ይህንን የሚያመላክቱ ይቅርታ ከሰባተኛው ክፍለዘመን ጀምሮ በስፋት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አይነቱ የልዕልና መገለጫ ያለምንም ተቃዎሞና ውጣውረድ ሲከናወን ቆይቷል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ከነገሥታቱ በተጨማሪ ሌሎች ስልጣን ያላቸው አካላት ለተከታዮቻቸው ይቅርታ በማድረግ ያላቸውን ስልጣን የነገሥታትን ያህል ማሳየት ይፈልጉ ስለነበር በዚህ ረገድ ሽኩቻዎች ታይተዋል፡፡ ለዚህ አይነተኛ ምሳሌ የሚሆነው በእንግሊዝ ካህናቱና ፓርላማው በየራሳቸው ልክ እንደንጉሱ ሁሉ ይቅርታ የማድረግን ስልጣን ተግባራዊ በማድረግ የንጉሡን ይቅርታ የመስጠት ስልጣን ለመቃወም ሞክረዋል፡፡[51] በአጭሩ ይቅርታ በነገሥታት ወይም በሀገር መሪዎች በግዛታቸው ወንጀል ፈጽመው ለተቀጡ ወንጀሎች በሕግ የተሰጣቸውን ስልጣን ወይም የገዥነታቸውን ችሮታ በመጠቀም ከእስራት እንዲለቀቁ የሚያደርጉበት አሰራር ነው፡፡

## 4. ይቅርታ በሌሎች አገሮች የወንጀል ፍትህ ሥርዓት

በዚህ ክፍል ይቅርታ በሌሎች አገሮች ምን ዓይነት የሕግ ይዘትና አፈጻጸም እንዳለው በአጭሩ መመልከቱ ወደፊት በኢትዮጵያ በተለይም በአማራ ብሄራዊ ክልል የፍትህ ሥርዓት ውስጥ ምን አይነት ቦታና አፈጻጸም እንዳለው ለመተንተን አቅም ሆኖ እንደሚያገለግል ይታመናል፡፡ በመሆኑም ይቅርታን አዘውትረው ከሚጠቀሙ አገሮች ውስጥ የቤልጅየም፣ የጀርመንና የስዊዘርላንድን የሕግ ማእቀፍና አፈጻጸም በናሙናነት ተመርጠው ተቃኝተዋል ፡፡

---

[48] H. Rept. Justice Undone: Clemency Decisions in the Clinton White House, Volume 1 - 107th Congress (2001-2002), available at https://www.congress.gov/congressional-report/107th-congress/house-report/454/3 last accessed on 10 August 2017.

[49] Kathleen Dean Moore, supra note 33, pp 16-18.

[50] ዝኒ ከማሁ፡፡

[51] ዝኒ ከማሁ፡፡

### *4.1 ቤልጅየም*

ቤልጅየም ይቅርታን በሕግ ማእቀፏ ውስጥ በማካተት ተግባራዊ ከሚያደርጉ የአውሮፓ አገሮች መካከል አንዷ ናት፡፡ አገሪቷ ይቅርታን የተመለከተ ድንጋጌ በ1994 ባወጣችው ሕገመንግሥት አስፍራለች፡፡[52] በዚህ ሕገመንግሥት መሠረት ይቅርታ የማድረግ ስልጣን ለንጉሱ የተሰጠ ሲሆን፣ ንጉሱ በፍርድ ቤቶች የተወሰነውን ቅጣት ሙሉ በሙሉ በመሰረዝ ወይም በከፊል በመቀነስ ለታራሚዎች ይቅርታ ሊያደርግ ይችላል፡፡[53] ይሁን እንጂ ይቅርታን በማድረግ ረገድ ስልጣኑን ያለአግባብ እንዳይጠቀም በዚሁ ሕገመንግሥት ገደብ ተጥሎበታል፡፡ የሚጣለውም ገደብ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ባሕርይ ያለው ይመስላል፡፡ የሀገሪቱ ሚኒስተሮችና ሌሎች ከፍተኛ ሹማምንት ወንጀል ፈጽመው በሀገሪቱ ጠቅላይ ፍርድቤት ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት በሚተላለፍባቸው ጊዜ የይቅርታ ተጠቃሚ ለመሆን ጥያቄው በሀገሪቱ ህዝብ ተወካዮች ምክርቤት ወይም በሕግ አውጭው አካል በኩል መቅረብ ይኖርበታል፡፡ በዚህ መንገድ የይቅርታው ጥያቄ ሲቀርብ ንጉሱ ይቅርታ ሊያደርግ ይችላል፡፡[54] ይህም ንጉሱ በራሱ ተነሳሽነትና ስልጣኑን ያለአግባብ በመገልገል በዘፈቀደ ወይም እንዳሻው ለሹማምንቱ ይቅርታን ከመስጠት ይገድበዋል፡፡

ሌላው ገደብ አስተዳደራዊ ሥነ-ሥርዓት የሚከተለው የይቅርታ አሰጣጥ ነው፡፡ ይህ አይነቱ የይቅርታ አሰጣጥ በረጅም ሥነ-ሥርዓት በብዙ የመንግሥት አካላት ካለፈ በኋላ የመጨረሻው ውሳኔ በንጉሱ አማካኝነት የሚጸድቅበት ወይም የሚሻርበት ሥርዓት ነው፡፡ የይቅርታ ጥያቄው ለንጉሱ፣ ለፍትህ ሚኒሰቴር ወይም በቀጥታ የይቅርታ አሰጣጥን ለሚያስተዳደረው *'the Service des Grâces'* እየተባለ ለሚጠራው የፍትህ ሚኒስቴሩ አካል ለሆነው መምሪያ (ዲፓርትሜንት) ሊቀርብ ይችላል፡፡ ከነዚህ የይቅርታ ጥያቄ አቀራረብ ሥርዓቶች በአንዱ የቀረበ ጥያቄ የይቅርታ አሰጣጥን በቀጥታ በሚከታተለው ዲፓርትሜንት በኩል አስፈላጊው ምርመራና ጥናት ከተደረገበት በኋላ መሰረታዊ መብቶችንና ነጻነቶችን ለሚከታተለው የፍትህ ሚኒስቴር ዲፓርትሜንት (the Directorate General of Legislative and Fundamental Rights and Liberties) ለአስተያየት ቀርቦ ከታየ በኋላ ከተገቢ አስተያየት ጋር ለአገሪቱ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እንዲላክ ይደረጋል፡፡ ይህ የደረሰው ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግም ጉዳዩን አጥንቶ ተገቢ ነው ከሚለው አስተያየት ጋር ወደፍትህ ሚኒስቴር ይመልሰዋል፡፡ ሚኒስቴር መስሪያቤቱም ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን የሶስቱን አካላት አጠቃላይ የጥናት ውጤት ቀምሮና የራሱን አስተያት ጨምሮ ይቅርታን ለማወጅ በሕገመንግስቱ ስልጣን ለተሰጠው የሀገሪቱ ንጉስ ያቀርባል፡፡ ንጉሱም ይቅርታውን ለማወጅ የታራሚውን ጉዳይ መመርመር ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ ወቅት በፍርድ ሂደት ያልታዩ አዳዲስ እውነታዎች ካሉ፣ ታራሚው ከጥፋተኝነት ውሳኔ በኋላ ባሕርይውን ለማሻሻል ያደረገው ጥረት ካለ፣ ከጥፋተኝነት ውሳኔ በኋላ ቅጣቱ ለመፈጸም የተፈጠረ የጊዜ መጓተትና ከፍርድ በፊት ታራሚው በሕገወጥ መንገድ ታስሮ ከሆነ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢ

---

[52] The Belgian Constitution, *Belgian State Gazette*, Belgian House of Representatives, (October 2012), Article 110, http://www.dekamer.be/kvvcr/pdf_sections/publications/constitution/grondwetEN.pdf last accessed on 1 May 2017.

[53] ዝኒ ከማሁ፡፡

[54] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 103፡፡

ነው የሚለውን ውሳኔ በቀረበለት የይቅርታ ውሳኔ ሐሳብ ላይ ያሳርፋል፡፡[55] እንዲህ ያለው አሰራር በንጉሱ ይቅርታ የመስጠት ስልጣን ላይ ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው የአስተዳደር አካላት እንደሚሳተፉበትና በስልጣን ያለአግባብ መገልገልን ሊቀንስ እንደሚችል የሚያሳይ አሰራር ነው፡፡

በቤልጅየም የሕግ ማእቀፍ ከፍ ብሎ በተመለከተው መልኩ ይቅርታ የሚሰጥ ሲሆን በዚህ አግባብ በርካታ ይቅርታዎች በንጉሱ አማካኝነት ተሰጥተዋል፡፡ የይቅርታ አፈጻጸሙ ሲታይ ቀደም ባሉት ዘመናት ለወንጀለኞቹ በጅምላ ህዝባዊ በዓልን በተለይም የንጉሱ ልደትና በአለሲመት ሲከበር ይቅርታ ሲሰጥ እንደነበር መገንዘብ ይቻላል፡፡ [56] ሆኖም የጅምላ የይቅርታ አሰጣጥ የታራሚዎችን ጉዳይ በተናጠል ለማየት የማያስችል መሆኑን በመገምገም ይቅርታው በተናጠል የሚሰጥበት አሰራር ተዘርግቷል፡፡ በዚህ መሠረት እያንዳንዱ ይቅርታ ጠያቂ ጉዳዩ በተናጠል እየታየ የይቅርታ ሥርዓቱ ተጠቃሚ የሚሆንበት አሰራር ተግባራዊ ሆኗል፡፡[57] በዚህ አሰራር መሠረት የይቅርታ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑ ታራሚዎች ቅጣታቸው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሊሰረዝላቸው ወይም በአመክሮ ሊለቀቁ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ታራሚዎች ለተበዳዩ ካሳ እንዲከፍሉ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሰጡ፣ ስልጠና እንዲከታተሉና ባሕርይያቸውን የማሻሻልና ከጥፋታቸው የመማር ግዴታ እንዲጣልባቸውም ይደረጋል፡፡[58]

## *4.2 ጀርመን*

ሌላዋ አውሮፓዊት አገር ጀርመን እንደሌሎች ሀገራት ይቅርታን በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓቷ በመተግበር ላይ ትገኛለች፡፡ ጀርመን የኮንቲኔንታል ሕግ ሥርዓት ከሚከተሉ የአለም ሀገራት መካከል አንዷ መሆኗና የፌዴራል መንግሥት አወቃቀር ሥርዓት መከተሏ ከኢትዮጵያ ጋር ያመሳስላታል፡፡ በይቅርታ ረገድም ሁለቱ ሃገሮች ተቀራራቢነት ያለው የሕግ ማእቀፍ ያላቸው በመሆኑ የኢትዮጵያን የይቅርታ አሰጣጥ ሕግና አፈጻጸሙን ከመመልከት በፊት የጀርመንን ሕግና ልምድ መመልከቱ አስተማሪነቱ የጎላ ሊሆን እንደሚችል ታምኖበታል፡፡ በመሆኑም የጀርመንን የይቅርታ ሕግና አፈጻጸም እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

ጀርመን ወንጀልን በግል ወይም በቡድን ፈጽመው በፍርድቤት ጥፋተኛ ለተባሉ ግለሰቦች ይቅርታ ለመስጠት የሚያስችል የሕግ ማእቀፍ አላት፡፡ በዚህ መሠረት የሀገሪቱ ፕሬዚዳንትና[59] የየክልሎቹ አስተዳዳሪዎች ይቅርታን የመስጠት ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡[60] ይህ ይቅርታ በብዛት ወንጀልን በተናጠል በፈጸሙና በፍርድቤት ቅጣት ለተወሰነባቸው ግለሰቦች የሚደረግ የይቅርታ አይነት ነው፡፡

---

[55] Pardons: European State Practices, Legal Memorandum March 2014, pp. 3-4.

[56] ዝኒ ከማሁ፡፡

[57] ዝኒ ከማሁ፡፡

[58] ዝኒ ከማሁ ገጽ 5፡፡

[59] Basic Law for the Federal Republic of Germany, Article 60 (2), last amended on 23 December 2014, as translated by Professor Christian Tomuschat and Professor David P. Currie, available at https://www.btg-bestellservice.de/pdf/80201000.pdf last accessed on 16 August 2017.

[60] Pardons: European State Practices, supra note 55, p. 5.

በሀገሪቱ ሕግ መሠረት በየደረጃው የሚገኙ መንግስታት ይቅርታን በሚሰጡበት ጊዜ ስልጣናቸውን ያለአግባብ እንዳይገለገሉ በሕግ ገደብ ተጥሎባቸዋል፡፡[61] ገደቦቹም ከቤልጅየሙ የይቅርታ ሕግና አሰራር በተለየ መልኩ የጀርመኑ ፕሬዚዳንት ወንጀልን በህብረት ለሰሩ ታራሚዎች ይቅርታ ማድረግ አለመቻሉ፣ ይቅርታ የመስጠት ስልጣኑ ለክልል መንግስታት ተከፍሎ መሰጠቱና በምርጫ ወቅት ፕሬዚዳንቱ ይቅርታን አስመልክቶ ያከናወናቸው ተግባራት ለህዝብ ትችት መቅረባቸው ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡[62] ይህንን የስልጣን ገደብ መሠረት በማድረግ ቅጣቱ ከፍርድ አላማው ጋር የማይጣጣም ከሆነና ከርትዐዊ ጋር የሚቃረን ሆኖ ሲገኝ ታራሚውን በይቅርታ እንዲለቀቅ በማድረግ የወንጀል ቅጣቱ ፍትሃዊና ርትዐዊ እንዲሆን የማድረግ ስራ ይከናወናል፡፡[63] ይህም ከይቅርታ መሰረታዊ አስተሳሰብ ጋር የሚጣጣምና በወንጀል ፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ ሊፈጸሙ ለሚችሉ ስህተቶች እንደመፍትሄ ሆኖ ያገለግላል፡፡

በጀርመን ይቅርታ እነዚህን መሰረታዊ ሃሳቦች መርህ በማድረግ የሚሰጥ ቢሆንም አሰራሩ አዘውትሮ ለህዝብ ይፋ አይደረግም፡፡ ይህንን አሰራር ሊያሻሽል በሚችል መልኩ ይቅርታ የተደረገላቸውን ታራሚዎች ይፋ በማድረግ ረገድ ተጠቃሽ የሚሆነው እ.አ.አ በ2003 ክላር የተባለ ለ20 አመታት በእስራት ከቆየ በኋላ ያቀረበው የይቅርታ ጥያቄንና ምክንያቱን ይፋ በማድረግ ይቅርታ ሊሰጥ ሞክሮ የነበረውና በህዝብና በመሪ የፖለቲካ ድርጅቶች ከፍተኛ ተቃውሞ የደረሰበት የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ሆረስት ኮሆልረ ነው፡፡[64]

### *4.3 ስዊዘርላንድ*

ስዊዘርላንድ ቀደምሲል ከተቃኙት አገሮችም ይሁን ከኢትዮጵያ ለየት ያለ የይቅርታ አሰጣጥ ሥርዓትን ዘርግታ ተግባር ላይ አውላለች፡፡ ይቅርታ የመስጠት ጽንሰሃሳብን እንደሌሎች አገሮች ሁሉ በሕገመንግስቷና በወንጀል ሕጎቿ ውስጥ አካትታ በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት እየፈጸሙ ላሉ ታራሚዎች ይቅርታን የምታደርግ ቢሆንም ይህንን ተግባራዊ የሚያደርጉ ተቋሞቿ አወቃቀራቸው ለየት ያለ ይዘት ያለው ነው፡፡ በዚች ሀገር ይቅርታን የመስጠት ስልጣን የተሰጠው በፌደራሉ መንግሥት ደረጃ የፌደራል አሴምብሊ ሲሆን በክልል ደረጃ ደግሞ ካንቶን በሚባለው አካል ነው፡፡ ሁለቱም አካላት እንደቅደምተከተላቸው በፌዴራልና በክልል ደረጃ ከሚገኙ ፓርላሜንት አባላት ተውጣጥተው ይቅርታን ለመስጠት የተቋቋሙ አደረጃጀቶች ናቸው፡፡[65] እነዚህ አካላት ይቅርታን ለመስጠት የቀረበውን የይቅርታ ጥያቄ በማጥናትና በማጣራት የሚያቀርብላቸው ተቋም ወይም ኮሚሽን የሚያዋቅሩ ሲሆን ይህ አሰራርም የሚሰጠውን የይቅርታ አይነት፣ ይቅርታ

[61] ዝኒ ከማሁ ገጽ 11-12፡፡

[62] ዝኒ ከማሁ፡፡

[63] ዝኒ ከማሁ፡፡

[64] Deutsche Welle, Statement by Convicted Terrorist Casts Doubt on Pardon (Feb. 26, 2007), available at http://www.dw.de/statement-by-convicted-terrorist-casts-doubt-on-pardon/a-2366065 last accessed on 16 August 2017

[65] Switzerland's Constitution of 1999 with Amendments through 2002, Article 173 (1) (k) (1999), available at http://www.admin.ch/ch/e/rs/1/101.en.pdf last accessed on August 16, 2017.

የሚሰጥበትን ምክንያትና ሁኔታ በመለየት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ የይቅርታ አሰጣጡ በኮሚሽኑ ከተጠና በኋላ ውጤቱ ለፌደራሉ ምክርቤት ቀርቦ በምክርቤቱ ፕሬዚዳንት አቅራቢነት በሸንጎው የድምጽ ብልጫ የይቅርታው ሁኔታ ይወሰናል፡፡[66]

## 5. ይቅርታ በኢትዮጵያ

የይቅርታ ሕጎችንና በባሕር ዳር ማረሚያቤት ያላቸውን አፈጻጸም ከማየት በፊት ይቅርታ በኢትዮጵያ ያለውን ጠቅላላ ገጽታ በአጭሩ መቃኘቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ይቅርታ በኢትዮጵያ ታሪክ ያለው ቦታ የቅርብ ጊዜ የሚባል አይደለም፡፡ በጥንታዊት ኢትዮጵያ ታሪክ ነገሥታት በጦር ያንበረከኳቸውንና የማረኳቸውን ተዋጊዎች ለተወሰነ ጊዜ ይዘው ካቆዩ በኋላ የተለያዩ በዓላት በሚከበሩበት ጊዜ በይቅርታና በምህረት ይለቁ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡[67] በዚህ ረገድ የመጀሪያውን የይቅርታ አዋጅ ያወጁት ንጉስ ኢዛና[68]፣ አለማየሁ የሚባል ልጃቸውን የልደት በዓል ምክንያት በማድረግ በርካታ ምርኮኞችን በይቅርታና ምህርት የለቀቁት አጼ ቴዎድሮስና[69] በተመሳሳይ ምርኮኞችን በይቅርታና ምህረት ሲለቁ የነበሩት አጼ ምኒሊክ ግንባርቀደም ተጠቃሽ ናቸው፡፡[70]

በዘመናዊ የኢትዮጵያ አስተዳደር ይቅርታ የሕግ እውቅና እንዲኖረው ተደርጎ ስራ ላይ ውሏል፡፡ በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዘመነመንግሥት ወጥተው ስራ ላይ የዋሉ ሕግጋት ይቅርታ የማድረግ ስልጣንን ለንጉሱ የሰጡ ናቸው፡፡ በ1931 እና በ1955 ዓ.ም የንጉሱን ፍጹማዊ ስልጣን ይዘው እንዲወጡ የተደረጉት ሕገመንግሥስታት እንደቅደምተከተላቸው በአንቀጽ 16 እና 35 ስር በኢትዮጵያ ሕገመንግሥት ታሪክ ውስጥ ይቅርታና ምህረት ቦታ እንዲኖራቸውና ሁለቱም በጽንሠሀሳብ ደረጃ ተለያይተው እንዲታወቁ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡[71] በ1949 ዓ.ም. የወጣው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ይቅርታ ለታራሚዎች ሊደረግ እንደሚችል በመደንገግ ጽንሰሃሳቡ በኢትዮጵያ ሕግ ይበልጥ ደምቆ እንዲነበብ አስችሏል፡፡[72] በ1980 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ ህዝባዊት ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት በተመሳሳይ ይቅርታን እንዲያካትት ተደርጓል፡፡ ሕገመንግሥቱ ይቅርታ የማድረግን ስልጣን ለሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ሰጥቷል፡፡[73] በኢፌዴሪ ሕገመንግሥትና የወንጀል ሕግም እንደቅደምተከተላቸው በአንቀጽ 71 እና 229 ይቅርታ ለታራሚዎች ሊደረግ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግም የይቅርታ አሰጣጥን የሚደነግጉ ወይም የሚወስኑ አዋጆችና መመሪያዎች በፌደራልና በክልል መንግስታት ወጥተው በስራ ላይ ውለዋል፡፡

---

[66] Pardons: European State Practices, Supra note 55, p. 9.

[67] Pankrust, Richard, *the economic history of Ethiopia from earlier time to 1800,* England,(1962), p. 28.

[68] *ዝኒ ከማሁ፡፡*

[69] *ዝኒ ከማሁ፡፡*

[70] *ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፤ ዓጼ ሚኒሊክ እና ኢትዮጵያ፣(*1903)፤ *ያልታተመ፣ገጽ* 8፡፡

[71] *ግርጌ ማስታወሻ ቁጥር* 19*ን ይመልከቱ፡፡*

[72] *የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር* 21*እንደተገለጸው፣ አንቀጽ* 239፡፡

[73] *የኢህዴሪ ህገመንግሥት፣አዋጅ ቁጥር* 1/1980፣ *ነጋሪት ጋዜጣ፣*( 1980)፣ *አንቀጽ* 86(3)(*መ*)፡፡

### 5.1. የይቅርታ ሕጎችና አፈጻጸማቸው በባሕር ዳር ማረሚያቤት

የይቅርታ ሕግን አውጥተው ተፈጻሚ እያደረጉ ካሉ ክልሎች መካከል አንዱ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት በመሆኑ የፌዴራሉና የዚህኑ ክልል ሕግጋት አጠቃላይ ይዘትና አፈጻጸም በባሕር ዳር ማረሚያቤት ምን እንደሚመስል ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርቧል፡፡

ከላይ ይቅርታ በኢትዮጵያ አጠቃላይ የሕግ ማእቀፍ ያለውን ቦታና ይዘት በአጭሩ ተቃኝቷል፡፡ ቀጥሎ ደግሞ የዚሁ የሕግ ማእቀፍ አካል የሆኑት የፌዴራሉና የአማራ ብሄራዊ ክልል የይቅርታ ሕጎች ይቅርታን ያዩበትን አግባብና ይዘት፣ ለአፈጻጸም እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ክፍተቶችን እንዲሁም በባሕር ዳር ማረሚያቤት የሚስተዋሉ የአፈጻጸም ችግሮችን ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡

የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት ይቅርታ የማድረግ ስልጣንን ለሀገሪቱ ርዕሰብሄር [74] የመስጠቱን ፈለግ ተከትሎ የተሻሻለው የክልሉ ሕገመንግሥት ይቅርታ የማድረግ ስልጣንን ለክልሉ መስተዳደር ምክርቤት ሰጥቷል፡፡ [75] በእነዚህ ሕገመንግሥታት መሠረት በፌዴራል መንግሥቱ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ርዕሰብሄሩ በአማራ ብሄራዊ ክልል መንግሥት የወንጀል ጉዳዮች ላይ ደግሞ የክልሉ መስተዳደር ምክርቤት ይቅርታ ያደርጋሉ፡፡ መንግሥታቱ በየሕገመንግሥታቸው የተሰጣቸውን ስልጣን ተግባራዊ ለማድረግ የይቅርታ አሰጣጥ ሥነሥርዓትን የሚደነግጉ አዋጆችና መመሪያዎችን አውጥተዋል፡፡ የፌዴራል መንግስቱ የተሻሻለውን የይቅርታ አዋጅ ቁጥር 840/2006[76] እና የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ደግሞ በ1998 ዓ.ም በክልሉ የይቅርታ አሰጣጥን ለመወሰን የሚያስችል አዋጅ[77] አውጥተው ስራ ላይ አውለዋል፡፡ አዋጆቹ በዋናነት ይቅርታ ስለሚሰጡ አካላትና የይቅርታ አሰጣጥና አፈጻጸሙን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን የያዙ ናቸው፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች ስር የተገለጹትን የይቅርታ ቅድመሁኔታዎችና ሥነሥርዓቶች መመልከቱ በይቅርታ አፈጻጸም ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉትን የሕግና የአተገባበር ችግሮች ለመለየት የጎላ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም የይቅርታ አሰጣጥና አፈጻጸም ድንጋጌዎቹ ያላቸውን ቅድመሁኔታና ሥነሥርዓት ከተግባራዊ አፈጻጸሙ ጋር በማያያዝ እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### 5.2 የይቅርታ ጥያቄ አቀራረብ

የይቅርታ ጥያቄ እንዴት ይቀርባል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ይቅርታ ለማንና ለምን እንደሚሰጥ በቅድሚያ መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡ በአማራ ክልል ይቅርታ የሚሰጥበትን ምክንያት ለመገንዘብ በፌዴራልና በክልሉ ደረጃ የወጡ አዋጆችን መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ሁለቱም አዋጆች በጋራ የሚያሰምሩበት ዐብይ የይቅርታ ዓላማ፤ "የይቅርታ አሰጣጥ ዋና ዓላማ የሕዝብን፣ የመንግሥትንና የታራሚዎችን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል መንግሥት የወንጀል ጥፋተኞች በጥፋታቸው የተጸጸቱና

---

[74] የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት፣አዋጅ ቁጥር 1/1987፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ (1987)፣ አንቀጽ 71(7) ( ከዚህ በኋላ የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት)፡፡

[75] የአማራ ብሄራዊ ክልል የተሻሻለው ሕገመንግሥት ማጽደቂ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 59/1994፣ዝክረ-ሕግ( 1994)፣፣ አንቀጽ 58(6) ( ከዚህ በኋላ የአብክመ ሕገመንግሥት)፡፡

[76] የፌዴራል የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 23 እንደተገለጸው፡፡

[77] የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ፣ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 24 እንደተገለጸው፡፡

የታረሙ መሆኑን በማረጋገጥ ወደ ህብረተሰቡ ተቀላቅለው አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ማድረግ ነው።"[78]; በሚል ቀርቧል።

ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ይቅርታ የሚሰጠው ታራሚዎች በፈጸሙት ወንጀል ተጸጽተው የባሕርይ ለውጥ በማድረግ የበደሉትን ማህበረሰብ እንዲክሱ ለማድረግ፣ ታራሚዎችን በማረሚያቤት በማቆየት በመንግሥትና በህዝብ ላይ ሊደርስ የሚችለውን የኢኮኖሚ ጫና ለመቀነስና በአጠቃላይ የሕዝብና የመንግሥትን ጥቅምና ደህንነት ለመጠበቅ እንደሆነ ነው። አዋጆቹ ይቅርታ የሕዝብን፣ የመንግሥትንና የታራሚዎችን ጥቅምና ደህንነት ግምት ውስጥ ያስገባ እንደሆነ በዓላማው ላይ ሲያመላክቱ የወንጀሉ ሰለባ የሆኑ የግል ተበዳዮችን ጥቅምና ደህንነት ከትኩረት አላስገቡም። የግል ተበዳዮችን ፍላጎትና ደህንነት በግልጽ ባለአመላከተ መልኩ የይቅርታ አላማ በአዋጆቹ መቀረጹ የወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ ለግል ተበዳዮች ተገቢውን ትኩረትና ቦታ አለመስጠቱን ያመላክታል። ሌላው ከይቅርታ አላማ ጋር ሊነሳ የሚገባው ነጥብ የአማራ ክልል የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ ከፌዴራል መንግስቱ አዋጅ ጋር ሲነጻጸር በይዘት ጠበብ ያለ መሆኑ ነው። የፌዴራል መንግሥቱ አዋጅ ይቅርታ የሚደረገው ለታራሚዎች፣ ለሕዝብና ለመንግሥት ጥቅም እንደሆነ ሲያመላክት የክልሉ ተነጻጻሪ ሕግ የሆነው አዋጅ ቁጥር 136/98 በአንቀጽ 3 ስር ያመላከተው የይቅርታ ዓላማ የታራሚዎችን ጥቅም የዘነጋ ይመስላል። ድንጋጌው የይቅርታን ዓላማ በሕዝብና በመንግሥት ጥቅም ላይ ብቻ ያነጻጸረ አድርጎ አቅርቦታል። ከዚህ በመነሳት የክልሉ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ በይዘት የሳሳና የጠበበ ሆኖ ይታያል።

በፌዴራል መንግስቱ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ አንቀጽ 3 ሥር የተመለከተው አላማ የታራሚዎችን፣ የሕዝብንና የመንግሥትን ጥቅምና ደህንነት መሠረት ያደረገ እንደመሆኑ መጠን ታራሚዎች በፍርድቤት ከተጣለባቸው ቅጣት በሕጉ የተመለከተውን ጊዜ በማረሚያቤት ካሳለፉ በኋላ የባሕርይ ለውጥ እንዳሳዩ ሲታመን የይቅርታ ጥያቄው በራሳቸው ወይም በሚመለከተው የመንግሥት አካል ለይቅርታ ቦርዱ ሊቀርብ ይችላል።[79] ይቅርታው በታራሚው በራሱ ወይም በባለቤቱ፣ በቅርብ ዘመዱ፣ በወኪሉ ወይም በጠበቃው አማካኝነት ሊቀርብ ይችላል።[80] ከዚህ ድንጋጌ የይቅርታ ጥያቄ አቅራቢዎች በቁጥር ብዙ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል። ይሁን እንጂ የይቅርታ ጥያቄው በራሱ በታራሚው ወይም የእሱ ሥልጣንና ፈቃድ በተሰጣቸው ወኪሎች ወይም ጠበቃዎች በኩል ካልቀረበ በባለቤቱ፣ በቅርብ ዘመዱ ወይም በሌላ ሰው አማካኝነት የሚቀርብ የይቅርታ ጥያቄ ይቅርታ የሚደረግለት ግለሰብ የሚስማማበት መሆኑን በፊርማው ማረጋገጥ እንዳለበት ይኸው ድንጋጌ ያዝዛል። ይህም የይቅርታ ጥያቄው ከታራሚው ከራሱ መመንጨት እንዳለበት ያስገነዝበናል። ሌላው የይቅርታ ጥያቄ የሚቀርብበት መንገድ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ለህዝብና ለመንግሥት ደህንነት ሲባል የይቅርታ ጥያቄ የሚያቀርቡበት አግባብ ነው። በቀድሞው የአገሪቱ ፍትህ ሚኒስቴር፣ በአሁኑ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ወይም የማረሚያቤቶች አስተዳደር ታራሚዎችን በመከታተል የባሕርይ ለውጥ ወይም መሻሻል አሳይተዋል

[78] የፌዴራል የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 23፣ አንቀጽ 3 እና የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ፣ ግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 24፣ አንቀጽ 3።
[79] የፌዴራል የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 23፣ አንቀጽ 15።
[80] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 15(2)።

*የሚሏቸውን በመምረጥ በይቅርታ እንዲለቀቁ ለይቅርታ ቦርድ ጥያቄውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡ እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ የይቅርታ ጥያቄው ማመልከቻ ግልባጭ ለታራሚው ደርሶት ፈቃደኛነቱን በፊርማው ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ታራሚው ማመልከቻው ከደረሰበት ቀን አንስቶ ባሉት 15 የስራ ቀናት ውስጥ ይቅርታውን እንደማይፈልግ ለቦርዱ በጽሑፍ ካልገለጸ እንደተቀበለው ተቆጥሮ የይቅርታው ተጠቃሚ ይሆናል፡፡*[81]

*ይህ የይቅርታ አቀራረብ መንገድ በአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ በአንቀጽ 11 ስር የተካተተ ቢሆንም፣ ከፌዴራሉ አዋጅ ጋር ሲነጻጸር መጠነኛ ልዩነቶች አሉት፡፡ ልዩነቶቹም የይቅርታ ጥያቄው በታራሚው ባለቤት፣ የቅርብ ዘመድ ወይም በሌላ ሰው አማካኝነት በሚቀርብበት ጊዜ ታራሚው ፈቃደኛነቱን በፊርማው እንዲያረጋግጥ የክልሉ አዋጅ አለመደንገጉና የይቅርታ ጥያቄው በክልሉ ፍትህ ቢሮና በማረሚያቤቶች አስተዳደር በኩል ሲቀርብ ሃሳቡ መቅረብ ያለበት ለክልሉ መንግሥት አስተዳደር ምክርቤት መሆኑ ነው፡፡*[82] *እነዚህ ልዩነቶች በአዋጁ ውስጥ የተፈጠሩት ለአሠራር አመችነት ታስቦ ነውን? የሚለው ጥያቄ መልስ የሚሻ ነጥብ እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡*

*ከእዚሁ ጋር ተያይዞ ጥያቄ የሚያጭረው ጉዳይ ይቅርታን ስለታራሚው ሆነው እንዲጠይቁ በአዋጁ የተፈቀደላቸው 'የቅርብ ዘመዶቹ'*[83] *እነማን ናቸው? የሚለው ነው፡፡ 'የቅርብ ዘመዶች' የሚለው አገላለጽ በኢትዮጵያ በተለይም በአማራ ባህልና ወግ ረዘም ያለ የዝምንድና ሐረግን የሚያሳይ በመሆኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የይቅርታን ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ዘመድ ማን እንደሆነ በግልጽ አልተመለከተም፡፡ ይህም ያለታራሚው እውቅናና ፈቃድ ይቅርታ ሊጠየቅ የሚችልበትን ሰፊ እድል የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ ለአፈጻጸምም አስቸጋሪ ነው፡፡ በተለይም የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ የይቅርታ ጥያቄ በቅርብ ዘመድ በሚቀርብበት ጊዜ የይቅርታ ተጠቃሚው እንዲያውቀውና ፈቃደኛ መሆኑን የሚያረጋግጥበት አሰራር አለመዘርጋቱ አፈጻጸሙን ይበልጥ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ያለይቅርታ ተጠቃሚው ፈቃድ የሚሰጥ ይቅርታ ምን ችግር ሊያስከትል ይችላል? የሚለው ጥያቄ እዚህ ላይ መነሳቱ አገባብነት ይኖረዋል፡፡ ከፍ ብሎ ባሉት የዚህ ጥናት ክፍሎች ለመግለጽ እንደተሞከረው ይቅርታ በበዳይና በተበዳይ መካከል ያለውን ግንኙነት ሰላማዊ የሚያደርግ እንደመሆኑ መጠን ይቅርታ የሚደረግለት ሰው በድርጊቱ ተጸጽቶና ጥፋቱን ተቀብሎ ተበዳዩን የሚክስበት መንገድ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የይቅርታ ተጠቃሚው ሙሉና ነጻ ፈቃድ ለይቅርታው ስኬታማነት ወሳኝ ሚና ይኖረዋል፡፡ ይቅርታ የሚደረግለት ሰው ሳያውቅና ሳይፈቅድ የሚደረግ ይቅርታ ባለቤት የለሽና የታለመውን ውጤት ሊያስገኝ የማይችል የይስሙላ ይቅርታ ይሆናል፡፡ ይቅርታው የታቀደውን ሰላም በማስገኘት ፋንታ ይቅርታውን*

[81] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 15(4፣ 5ና 6)፡፡

[82] የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ፣ ግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 24፣አንቀጽ 11(1 እና 2)፤ *"[ቃ]በክልሉ ስልጣን ስር በሚወድቅ ማናቸውም የወን[ጀን] ጉዳይ በፍርድቤት ተከሶ የመጨረሻ ፍርድ የተውሰነበት ማንኛውም ሰው የተወሰነ ፍርድ በሕግ በሕግ ይቅርታን የሚያስከለክል ካልሆነ በቀር የይቅርታ ጥያቄውን በራሱ፣ በባለቤቱ፣ በቅርብ ዘመዶቹ፣ በወኪሉ ወይም በጠበቃው አማካኝነት ማቅረብ ይችላል"፡፡ "[ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀፅ 1 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የክልሉ ፍትህ ቢሮ ወይም የማረሚያቤቶች አስ/ጽ/ ቤት ይቅርታ ሊደረግላቸው 2. የሚገባውን ሰዎች በመምረጥ ይቅርታ እንዲደረግላቸው ለክልሉ መስተዳደር ምክርቤት ሃሳብ ሊያቀርቡ ይችላል፡፡ መሥሪያቤቶች የይቅርታ ጥያቄ ለማቅረብ የወሰኑ እንደሆነ የይቅርታ መጠየቂያውን ደብዳቤ ቅጂ በስሙ ይቅርታ ለተጠየቀለት ሰው እንዲደርሰው ማድረግ ይኖርበታል"*

[83] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 11 (1)፡፡

በሰጠውና በይቅርታው ተጠቃሚ መካከል አለመግባባትንና ንትርክን ከመፍጠሩም በተጨማሪ የህዝብ አመኔታን ይሸረሽራል፡፡[84]

## 5.3 የይቅርታ አሰጣጥ ሂደት

የይቅርታ ጥያቄ ከላይ ከተመለከትናቸው የይቅርታ ጥያቄ ማቅረቢያ መንገዶች በአንዱ በጽሑፍ ለይቅርታ ቦርዱ የቀረበ እንደሆነ ቦርዱ ማመልከቻውን በአግባቡ መርምሮ ውሳኔ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ የይቅርታ ጥያቄ ማመልከቻው ይቅርታ ስለሚደረግለት ሰው ሊይዝ የሚገባቸው መረጃዎች በአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅና መመሪያ ተዘርዝረዋል፡፡ [85] በአዋጁና በመመሪያው የተመለከቱትን መስፈርቶች አሟልቶ የቀረበ የይቅርታ መጠየቂያ ማመልከቻ ፍርዱ ከተሰጠ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ሊታይ ይችላል፡፡ [86] አስፈላጊውን መረጃ ይዞ የቀረበ ማመልከቻ ሁሉ አወንታዊ መልስ እንደሚያገኝ ይታመናል፡፡ [87] በሌላ አነጋገር ከፍርድ በኋላ አስፈላጊውን መረጃ የያዘ ማመልከቻ ያቀረበ ታራሚ በመመሪያው ላይ የተመለከቱትን ዝርዝር ቅድመሁኔታዎች እስካላሟላ ድረስ የይቅርታ ተጠቃሚ አይሆንም፡፡ ለመሆኑ መሟላት ያለባቸው ቅድመሁኔታዎች ምንድን ናቸው? ይህንን ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ የአብክመን የይቅርታ አሰጣጥ ሥነሥርዓት መወሰኛ አዋጅ ለማስፈጸም የወጣውን መመሪያ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ በመመሪያው መሠረት ለአንድ ታራሚ የይቅርታ ተጠቃሚ መሆን መሟላት ያለባቸው ቅድመሁኔታዎች የባሕርይ መሻሻልን[88]፣ እድሜን[89]፣ የጤና ሁኔታን[90]፣ ጾታን [91] ፣ የእስራት መጠንና የእስር ቆይታ ጊዜን መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡ እነዚህን ቅድመሁኔታዎች አንድ በአንድ ከዚህ በታች ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

የባሕርይ መሻሻል ወይም ለውጥ በመመሪያው የይቅርታ ተጠቃሚ ለመሆን ከቅድመሁኔታዎቹ አንዱ ሆኖ ተመልክቷል፡፡ [92] ይሁን እንጂ ዝርዝር አፈጻጸሙ እንደሌሎቹ መስፈርቶች በመመሪያው በግልጽ አልተመለከተም፡፡ አንድ ታራሚ የይቅርታ ተጠቃሚ ለመሆን የባሕርይ መሻሻል ወይም ለውጥ አሳይቷል ለማለት የሚያስችል ዝርዝር መመዘኛ በሌለበት ቅድመሁኔታውን አሟልቷል ወይም አላሟላም ለማለት ያስቸግራል፡፡ ይህም በመሆኑ የዚህ ጥናት ትኩረት በሆነው በባሕር ዳር ማረሚያቤት ከማረሚያቤቱ ባለሙያዎች ጋር በተደረጉ የቡድን

---

[84] Ethiopia Frees opposition leader Birtukan Mideksa, available at https://www.theguardian.com/world/2010/oct/06/ethiopia-frees-opposition-leader-birtukan-mideksa last accessed 13 December 2017

[85] የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ፣ ግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 24፣ አንቀጽ 12፤ የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ መመሪያ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 25 እንደተገለጸው፡፡

[86] የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ፣ ግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 24፣ አንቀጽ 15 እና የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ መመሪያ ፣ ግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 25፣ አንቀጽ 13 ይመልከቱ፡፡

[87] ከአብክመ ማረሚያቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን የተገኘ የ 2009 ዓ.ም ሪፖርት እንደሚያሳየው በአመቱ በአዲስ አመት መገቢያና በግንቦት 20 በዓል 157 ሴት ታራሚዎችና 5421 ወንድ ታራሚዎች በይቅርታ ከእስር ተለቀዋል፡፡

[88] የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ፣ ግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 24፣ አንቀጽ 20 እና የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ መመሪያ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 25፣አንቀጽ 5፡፡

[89] የፌዴራል የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 23፣ አንቀጽ 20፡፡

[90] ዝኒ ከማሁ፡፡

[91] የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ መመሪያ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 25፣ ቁጥር 6፡፡

[92] ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 5፡፡

ውይይቶች ባለሙያዎቹ በክልሉ አመክሮ አሰጣጥ መመሪያ የተመለከተውን ዝርዝር የባሕርይ ለውጥ መለኪያ ለመጠቀም እንደተገደዱ ገልጸዋል፡፡[93]

ከባሕርይ መሻሻል ወይም ለውጥ በተጨማሪ ከእድሜ፣ ከጾታ፣ ከጤናና ከሌሎችም የታራሚው የግል ሁኔታ አንጻር እየታየ ፍርድ ቤቱ ካስተላለፈበት የእስራት መጠን ምን ያህሉን ሲፈጽም የይቅርታ ተጠቃሚ እንደሚሆን ተመልክቷል፡፡[94] መመሪያው በወንጀል ሕጉ ከተመለከተው ከፍተኛ የእስራት መጠን ወይም ጣሪያ ማለትም ከእድሜ ልክ እስራት ጀምሮ እስከዝቅተኛው ቀላል እስራት ጊዜ ድረስ ጾታን መሠረት ያደረገ የአቀናነስ ሥርዓት አለው፡፡ [95] በዚህ አሰራር መሠረት ሴት ታራሚዎች በይቅርታ አሰጣጡ የልዩ መብት ተጠቃሚዎች ሆነዋል፡፡ አንዲት ሴት ታራሚና አንድ ወንድ ታራሚ ከአንድ አመት በላይ የሆነ እኩል የእስራት ቅጣት ቢወሰንባቸው የይቅርታ ተጠቃሚ ለመሆን ሴቷ በማረሚያቤት የሚኖራት ቆይታ ወይም የቅጣት ፍርድ አፈጻጸም ከወንድ ታራሚው አንጻር ሲታይ ያነሰ መሆን እንዳለበት መመሪያው ያመላክታል፡፡ [96] ለሴት ታራሚዎች የይቅርታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በፍርድቤት ከተላለፈባቸው የእስራት መጠን በአማካይ ከአንድ እስከሁለት አመት በተመሳሳይ ወንጀልና እስራት ከተፈረደባቸው ወንድ ታራሚዎች እንዲቀነስላቸው በመመሪያው ተመልክቷል፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ወንድና አንዲት ሴት እኩል የእድሜ ልክ እስራት ቢፈረድባቸው ከእዚህ ውስጥ ወንዱ 14 አመት ሴቷ 12 አመት በማረሚያቤት ከቆዩና የባሕርይ ለውጥ ካመጡ ሌሎች መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የይቅርታ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ [97] በሌላ በኩል መሰል ታራሚዎች ከአንድ አመት በታች እስራት ቢፈረድባቸው ሴቷ 1/3ኛውን ወንዱ ደግሞ ግማሹን የእስራት ጊዜ ካጠናቀቁ ሌሎች መስፈርቶች ከተሟሉ የይቅርታ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡ [98] ሆኖም ሴቷ ታራሚ ነፍሰጡር ከሆነች በልዩ ሁኔታ የይቅርታው ተጠቃሚ እንድትሆን መመሪያው ይፈቅዳል፡፡[99] ከፍ ብሎ እንደአብነት በተመለከትናቸው ከፍተኛና ዝቅተኛ የእስራት ፍርዶች ላይ የተመለከተው ስሌት በሌሎቹ የእስራት መጠኖችም ላይ ሲተገበር በጠቅላላው ለሴት ታራሚዎች ከአንድ እስከሁለት አመት ሊደርስ የሚችል የእስራት መጠን ቅናሽ ይደረግላቸዋል፡፡

ከእድሜ አንጻርም መመሪያው በወጣት አጥፊዎችና በእድሜ የገፉ ታራሚዎች በይቅርታ እንዲወጡ ለማድረግ የተለየ መስፈርት አለው፡፡ እድሜያቸው ከ9 -15 አመት የሆኑ ወጣት አጥፊዎች ሦስት ዓመትና ከዚያ በለይ የሆነ እስራት ከተፈረደባቸው ከዚህ ውስጥ 1/3ኛውን፣ ከ3 ዓመት በታች ከተፈረደባቸው ደግሞ 1/4ኛውን ከፈጸሙና ሌሎችን መስፈርቶች አሟልተው ከተገኙ የይቅርታ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡ [100] በእድሜ የገፉ ታራሚዎች እንደሴት ታራሚዎችና እንደወጣቱ ሁሉ በመመሪያው በልዩ ሁኔታ በይቅርታ ወቅት እንዲስተናገዱ

---

[93] በባሕር ዳር ማረሚያቤት ከሚገኙ ባለሙያዎች ጋር ስለ ይቅርታ አሰጣጥ ከተደረገ ቡድን ዉይይት የተገኘ፣ ግንቦት 2008 ዓ.ም፣ ለበለጠ ግንዛቤ በአብክመ አስተዳደርና ጸጥታ ቢሮ የአመክሮ አሰጣጥ ስርዓትንና አፈጻጸምን ለመወሰን የወጣ ጊዚያዊ መመሪያ ቁጥር 1/2003 ዓ.ም ይመልከቱ፡፡

[94] የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ መመሪያ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 25፣ ቁጥር 5፡፡

[95] ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 5 ይመልከቱ፡፡

[96] ዝኒ ከማሁ፡፡

[97] ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 5(1)፡፡

[98] ዝኒ ከማሁ፣ቁጥር 5(8)፡፡

[99] ዝኒ ከማሁ፣ቁጥር 6(6ና 7)፡፡

[100] ዝኒ ከማሁ፣ቁጥር 6(1ና 2)፡፡

ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሠረት እድሜው ከ55 ዓመት በላይ የሆነ ወንድ ታራሚና እድሜዋ 50 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ ሴት ታራሚ ከተጣለባቸው የእድሜ ልክ እስራት 12 እና 11 ዓመት እንደቅደምተከተላቸው ፈጽመው ከተገኙ የይቅርታ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡[101] እነዚሁ ታራሚዎች ሦስት ዓመት በላይ በሆነ እስራት ከተቀጡ 1/3ኛውን፤ ቅጣቱ ከእዚህ በታች የሆነ እንደሆነ 1/4ኛውን በተመሳሳይ መፈጸም ይጠበቅባቸዋል፡፡[102]

ከላይ ከተቃኙት የይቅርታ መስፈርቶች በተጨማሪ በመመሪያው የተመለከተው መስፈርት የታራሚው የጤና ሁኔታ ነው፡፡ ታራሚው የአእምሮ ህመምተኛ፣ የማይድኑ በሽታዎች ለምሳሌ፣ ስኳር፣ ኤች አይቪ ኤድስ፣ ካንሰርና ሌሎችም በሽታዎች ተጠቂ የሆነ እንደሆነና የእለት ተዕለት ተግባሩን ለማከናወን የሚቸገር የአካልጉዳተኛ የሆነ ሰው የእስራት መጠኑ ከግምት ውስጥ ሳይገባ የይቅርታ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡[103] ይሁን እንጂ የይቅርታ ተጠቃሚው የጤና ሁኔታ ህጋዊነት ካለው የጤና ተቋም ማስረጃ ማቅረብን እንደቅድመሁኔታ ይጠይቃል፡፡ የአዕምሮ ህመምን በተመለከተ በሀገሪቱ ካለው የአእምሮ ህክምና ተቋም ከሆነው አማኑኤል ሆስፒታል ወይም ከሌላ ተነጻጻሪ ተቋም ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት መመሪያው ያዝዛል፡፡[104] ከዚህ ላይ የዘርፉ ባለሙያዎች መልስ የሚሹ ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎችን ያነሳሉ፡፡ እነሱም ተነጻጻሪ ሆስፒታል ምን ማለት ነው? ማስረጃውን የሚያቀርበው ማን ነው? የሚሉ ናቸው፡፡ ስለታራሚው የአእምሮ ህምም ማስረጃ ሊሰጥ በሚገባው የህክምና ተቋም ወይም ሆስፒታል የአፈጻጸም ችግር የሚስተዋል ሲሆን ይኸውም በክልሉ የሚገኙ ከፍተኛ ሆስፒታሎች ከአማኑኤል የአዕምሮ ህክምና ሆስፒታል ጋር ተነጻጻሪ ተደርገው የሚሰጡት ማስረጃ በይቅርታ ቦርዱ በኩል አንዳንድ ጊዜ ተቀባይነት ሲያገኝ ሌላ ጊዜ ውድቅ እየተደረገ በአሰራሩ ላይ የወጥነት ችግር በመፍጠር ላይ ይገኛል፡፡ በእዚህ ምክንያትም የአእምሮ ህመም ችግር ያለባቸው ታራሚዎች የይቅርታ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ በመደረጉ በማረሚያቤቱ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ሲያሳርፉ ይስተዋላል፡፡[105] በአጠቃላይ የታራሚው ጤንነት ሁኔታ ለይቅርታ ተጠቃሚነት ወሳኝ መስፈርት ቢሆንም በአፈጻጸም ረገድ ከላይ የተወሱት ጥያቄዎችና ሌሎችም ችግሮች[106] የሚስተዋሉበት ነው፡፡

በመጨረሻም ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት ሁኔታ በይቅርታ ጠያቂውና በግል ተበዳይ ወይም በቅርብ ቤተሰቦቹ መካከል ሊፈጸም የሚገባው የእርቅ ጉዳይ ነው፡፡ ምንም እንኳ መመሪያው እርቅን በሁሉም የወንጀል ጉዳዮች ላይ እንደቅድመመስፈርት ባያመላክከትም በሰው መግደልና በመግደል ሙከራ ወንጀልን በተመለከተ በማህበረሰቡና በወንጀሉ ሰለባ በሆኑ ግለሰቦች ላይ ጥሎ የሚያልፈውን ቁርሾ በመሻር ረገድ የሚኖረውን ፋይዳ በመገንዘብ ይቅርታ ጠያቂው እርቅን

---

[101] ዝኒ ከማሁ፣ቁጥር 6(3)፡፡

[102] ዝኒ ከማሁ፣ቁጥር 6(4ና 5)፡፡

[103] ዝኒ ከማሁ፣ቁጥር 7፡፡

[104] ዝኒ ከማሁ፡፡

[105] ኮማንደር አማረ ወርቁ አይናለም፣ በአብክመ ማረሚያቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ታራሚዎች አያያዝ አስተዳደር ዋና የስራ ሂደት፣ ስለይቅርታ አሰጣጥ የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ ሐምሌ 2009፡፡

[106] ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚስተዋሉ ችግሮች አስተዳደራዊ ሲሆኑ እነዚህም የመጓጓዣ፣ የበጀት፣ ታራሚውን አጅቦ ወደህክምና ተቋም የሚወስድ የሰው ኃይል፣ የውሎ አበል አከፋፈል መሆናቸውን በጥናቱ ከተመረጡ የመረጃ ምንጮች መገንዘብ ተችሏል፡፡

አስቀድሞ መፈጸም እንዳለበት በግልጽ ደንግጓል። [107] እርቁ መፈጸም ያለበት በይቅርታ ጠያቂውና በሟች የቅርብ ዘመዶች ወይም በግል ተበዳይ መካከል እንደሆነ መመሪያው ያመላክታል። [108] እርቅ መፈጸሙ ብቻ ሳይሆን እንደጉዳቱ መጠን በካሳ መልክ እንደአየአካባቢው ባህልና ልምድ ገንዘብ ሊከፈል እንደሚገባም በመመሪያው ተገልጿል። የገንዘቡ መጠንም የተጋነነ መሆን እንደሌለበት ይኸው መመሪያ ደንግጓል። [109] ሆኖም እርቅ እንዲፈጽም የተጠየቀው ወገን ከአካባቢው ባህል ውጭ በሆነ መንገድ የተጋነነ የገንዘብ መጠን ከጠየቀ ወይም እርቅ ሊፈጽሙ የሚገባቸው ሰዎች በአካባቢው አለመኖራቸው ወንጀሉ በተፈጸመበት ወረዳ አስተዳደርና ጸጥታ ጉዳይ ጽ/ቤት ከተረጋገጠ ይህ ቅድመሁኔታ ሳይሟላ ይቅርታ የጠየቀው ታራሚ የይቅርታው ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል። [110] ታራሚዎች በማረሚያቤት ሆነው ከማረሚያቤት ውጭ ካሉ ተበዳዮች ጋር እርቅ እንዲፈጽሙና ካሳ እንዲከፍሉ እንደቅድመሁኔታ የመቅረቡ ጉዳይ እርቁን በተሟላ ሁኔታ ለማስፈጸም በርካታ ችግሮች እንዲከሰቱ ምክንያት ሆኗል። ዋና ዋና ችግሮችም እርቅን ለመፈጸም ተገቢው የተበዳይ ዘመድ ማን እንደሆነ በመመሪያው በግልጽ ካለመመልከቱና ለእርቁ ከሚጠየቀው የገንዘብ መጠን ጋር የተያያዙ ናቸው።

የተጎጅ ቤተሰቦች እነማን ናቸው? የሚለው በዘር ሐረጋቸው ቅደምተከተል በመመሪያው የትርጉም ክፍል ይገለጽ እንጂ እርቅን በመፈጸም ረገድ ማን የቀዳሚነት መብት አለው? የሚለው በግልጽ አልተመለከተም። ይህ በመሆኑ በተለያዩ ደረጃዎች ያሉ የስራ ኃላፊዎችም ይሁን ባለሙያዎች አንድ አይነት ሐሳብ ወይም አተረጓጎም የላቸውም። አንዳንዶቹ በመመሪያው ላይ ከተመለከቱት የተጎጅ ቤተሰቦች መካከል አንዱ እርቅ መፈጸሙ ታራሚውን የይቅርታ ተጠቃሚ ማድረግ ይችላል [111] ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ ሁሉም የቤተሰብ አባላት መታረቅና በመካከላቸው ስምምነት መፍጠር ካልተቻለ ታራሚውን የይቅርታ ተጠቃሚ ማድረግ አይቻልም [112] በማለት ይሟገታሉ። ሌሎች የዘርፉ ባለሙያዎችም የተጎጂ ባለቤት ወይም በእድሜ ትልቁ ልጅ መታረቁ ሌሎቹን ማሳመን ስለሚችሉ በቂ ነው ይላሉ። [113] እነዚህ ሁሉ ሃሳቦች በትግበራ ወቅት ስለሚነሱ የይቅርታ አፈጻጸሙን ወጥ እንዳይሆን እንዳደረጉት መገንዘብ ይቻላል።

ከእርቅ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉ ሌሎች ችግሮች፣ የእርቅ ሂደቱ ከማረሚያቤት ተጀምሮ ተበዳዮች ካሉበት ቀበሌ ስለሚፈጸም ሂደቱ ረጅም መሆኑ፣ አስታራቂ ኮሚቴዎች በአግባቡ አለመፈጸማቸው፣ ተበዳዮችንና ቤተሰቦቻቸውን ለማግኘት (በተለይም ሂደቱን የሚከታተል የይቅርታ ጠያቂው ቤተሰብ በሌለበት

---

[107] የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ መመሪያ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 25፣ ቁጥር 11።

[108] ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 11(1)።

[109] ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 11(1) እና (2) ይመልከቱ።

[110] ዝኒ ከማሁ፣ቁጥር 11።

[111] ኮማንደር እውነቱ፣ በአብክመ ማረሚያቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን የታራሚዎች አያያዝ አስተዳደር ባለሙያ፣ ስለይቅርታ አሰጣጥ የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ ግንቦት 2008 ዓ.ም.።

[112] አቶ ሐይሉ አስምር፣ በአብክመ የይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት ባለሙያ፣ ስለይቅርታ አሰጣጥ የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ መጋቢት 2009።

[113] አቶ ገብረ-መስቀል ደምሌ፣ በአብክመ ይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት ባለሙያ፣ ስለይቅርታ አሰጣጥ የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ መጋቢት 2009 እና በባሕር ዳር ማረሚያቤት ከሚገኙ ባለሙያዎችና የስራ ኃላፊዎች ጋር ስለይቅርታ አሰጣጥ የተደረገ የቡድን ውይይት፣ ሚያዝያ 2008 ዓ.ም.።

ጊዜ) አለመቻላቸውና ይቅርታ ጠያቂዎቹ ለአስታራቂ ኮሚቴው አበልና የሥራ ማስኬጃ እንዲከፍሉ መገደዳቸው ናቸው፡፡[114]

በመመሪያው እርቅ በሚያስፈልጋቸው የወንጀል ጉዳዮች ጥፋተኛ ተብለው የታሰሩ ታራሚዎች የይቅርታ ተጠቃሚ ለመሆን እርቅን በሚፈጽሙበት ጊዜ እንደአካባቢው ባህልና ልምድ የሚጠየቀውን ገንዘብ መክፈል እንዳለባቸው መመልከቱ ቀደምሲል ተወስቷል፡፡ በዚህም መሠረት የግል ተበዳዮች ወይም የሟች የቅርብ ዘመዶች ለደረሰባቸው በደል መካሻ የሚጠይቁት የገንዘብ መጠን መጋን እንደሌለበት መመሪያው ቢገልጽም በተግባር ግን ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ክፍያን በመጠየቅ እርቁን ሲያስተጓጉሉና ታራሚዎች የይቅርታ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ሲያደርጉ ይስተዋላል፡፡ [115] እንዲህ አይነት ችግር ሲያጋጥምና የግል ተበዳዮች ለእርቅ ፍቃደኛ አለመሆናቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ወንጀሉ በተፈጸመበት ወረዳ አስተዳደርና ፀጥታ ጽ/ቤት በኩል ሲቀርብ የይቅርታ ቦርዱ ታራሚዎቹን የይቅርታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ እንዳለበት መመሪያው በግለጽ ቢያመላክትም በተግባር ይህ ባለመፈጸሙ በርካታ ታራሚዎች በዚሁ ምክንያት ብቻ የይቅርታ ተጠቃሚ መሆን እንዳልቻሉ ተስተውሏል፡፡ [116] ለአብነትም በ2009 ዓ.ም በአማራ ክልል በሚገኙ ማረሚያቤቶች ካሉ ታራሚዎች 2400 የሚሆኑት እርቅ የጠየቁ ሲሆን፣ 829 ታራሚዎች ብቻ እርቅን መፈጸም ችለዋል፡፡ ቀሪዎቹ በአፈጻጸም ችግር እርቅን ሳይፈጽሙ ቀርተዋል፡፡ እርቅ ካልፈጸሙ ታራሚዎች መካከል 155 የሚሆኑት ያቀረቡት የይቅርታ ጥያቄና ማስረጃ በቦርዱ ተቀባይነትን ባለማግኘቱ የይቅርታ ተጠቃሚ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡ [117] በአጠቃላይ ከእርቅ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉ ችግሮች በባሕር ዳር ማረሚያቤት የይቅርታ አሰጣጥ ሂደት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ በማድረስ ላይ እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ የተቃኙት የእድሜ፣ የጾታ፣ የጤናና ሌሎች ቅድመሁኔታዎች በጠቅላላው ሲታዩ የእስራት ቅጣትን ለማስቀነስ እንደምክንያት የተወሰዱ በመሆናቸው የይቅርታ ተጠቃሚ የሚሆኑት በእስራት የተቀጡ ታራሚዎች ብቻ እንደሆኑ ያመላክታል ፡፡ ይህ ሁኔታ በወንጀል ሕጉም ሆነ በፌዴራሉና በአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጆች በይቅርታ ሊቀነስ ወይም ሊሻሻል የሚችለው ማንኛውም የቅጣት አይነት እንደሆነ የገለጹ ቢሆንም መመሪያው የእስራት ቅጣት ላይ ብቻ ያነጣጠረና ሌሎች የቅጣት አይነቶች በይቅርታ ሊቀነሱ ወይም ሊሻሻሉ እንደማይችሉ በማመላከቱ በአዋጆቹና በመመሪያው መካከል ልዩነትን የፈጠረ ይመስላል፡፡ [118]

---

[114] በባሕር ዳር ማረሚያቤት ከሚገኙ ታራሚዎች ጋር ስለይቅርታ አሰጣጥ የተደረገ የቡድን ውይይት፣ ግንቦት 2008 ዓ.ም.፡፡

[115] ዝኒ ከማሁ፡፡

[116] ዝኒ ከማሁ፡፡

[117] ኮማንደር አማረ፣ በግርጌ ማስታወሻ 104 እንደተገለጸው፡፡

[118] የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 1፣ አንቀጽ 229፣
የኢፌዴሪ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ፣ ግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 23

**አንቀጽ 2**

*(1) "ይቅርታ" ማለት የቅጣት ፍርድ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ወይም የቅጣት ፍርዱ አፈፃፀምና ዓይነት ቀለል ተደርጎ እንዲፈፀም ማድረግ ነው፤*

*(2) "የቅጣት ፍርድ" ማለት በወንጀል ጉዳይ ዋና ቅጣትን፣ተጨማሪ ቅጣትን ወይም የክልከላና የጥበቃ ጥንቃቄ እርምጃን በተመለከተ በፍርድቤት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ነው፤*

የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ፣ ግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 24

**አንቀጽ 2**

በተግባር የሚታየውም በይቅርታ አማካኝነት ታራሚዎች ከእስር ሲለቀቁ እንጂ ሌሎች የቅጣት አይነቶች ሲሻሻሉላቸው ወይም ሲቀነሱላቸው አይደለም፡፡ በመሆኑም ይቅርታ በወንጀል ሕጉና በይቅርታ አዋጆቹ በተመለከተው መሠረት በእስራት ቅጣት ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎቹ የቅጣት አይነቶችም ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል፡፡

## *5.4 ይቅርታን የሚያስከለክሉ ሁኔታዎች*

የይቅርታ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስፈልጉ ቅድመሁኔታዎች ከፍ ብሎ የተገለጹ ሲሆን ከዚሁ ጋር በንጽጽር መታየት የሚገባው ነጥብ ይቅርታን ሊያስከለክሉ የሚችሉ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? የሚለው ነው፡፡ ቅድመሁኔታዎችን ማሟላት የይቅርታ ተጠቃሚ ለመሆን እንደመስፈርት በመመሪያው ቢመለከትም እነዚህን ማሟላት ብቻውን በቂ አለመሆኑን የሚያሳይ ልዩ ሁኔታ በመመሪያው ተደንግጓል፡፡ በሀገሪቱ ይቅርታ ሊደረግላቸው አይገባም ተብለው የታመኑ የወንጀል አይነቶችና ወንጀል ፈጻሚዎች ተለይተው በሕገመንግሥቱና በመመሪያው ተገልጸዋል፡፡ በሰው ልጆች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣ የሰው ዘር ማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ መውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን መሰወርና ኢሰብአዊ የሆነ የድብደባ ድርጊት መፈጸም በኢፌዴሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 28 መሠረት ይቅርታ አይደረግላቸውም፡፡ [119] በይቅርታ አሰጣጥ መመሪያው መሠረት ደግሞ በርካታ የወንጀል አይነቶች ይቅርታ እንደሚያስከለክሉ የተደነገገ ሲሆን ዋና ዋናዎቹም፣ የሙስና ወንጀል፣ ሽብርተኝነት ፣ ውንብድና፣ አስገድዶ መድፈር፣ ግብረሰዶም፣ የሐሰት ገንዘብ መስራት ወይም ማዘዋወር፣ በጦር መሳሪያ መነገድ ና ሌሎችም ናቸው፡፡[120]

ይቅርታ ለሚያስከለክሉ ወንጀሎች እንደምክንያት የሚቀርቡት፤ ወንጀሎቹ በህዝብና በመንግሥት ጥቅም ላይ የሚያደርሱት ጉዳት እጅግ በጣም ከፍተኛ መሆኑ፣ በመሰል ወንጀሎች ላይ የሚሳተፉ ወንጀለኞች ባሕርይ አደገኛነትና የወንጀለኞቹን ባሕርይ ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል የማረሚያቤቶችን የረዥም ጊዜ ክትትልና ጥረት የሚሻ መሆኑ ናቸው፡፡ [121] ይሁን እንጂ ይቅርታ የሚያስከለክሉ ወንጀሎች ከፍ ብሎ የተገለጹትን ምክንያቶች ግምት ውስጥ ያስገቡ ከሆነ አስገድዶ መድፈርና ግብረሰዶም የመሳሰሉ በግለሰቦች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ይቅርታን ሲያስከለክሉ በግፍ ሰው መግደልን ያህል ከባድ ወንጀል ይቅርታን ለማስከልከል እንደምክንያት ተቆጥሮ በመመሪያው ውስጥ አለመካተቱ ጥያቄን ያጭራል፡፡ ሌላው በጥያቄ መልክ መነሳት ያለበት የሽብርተኝነት ወንጀል [122] ፣ ሐሰተኛ ገንዘብ መስራት ወይም ማዘዋወር [123] ፣ አደገኛ እፅ ማምረት፣ ማዘዋወር፣ ይዞ መገኘት ወይም

1. *"የይቅርታ ጥያቄ" ማለት አንድ ፍርድ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ወይም የቅጣት አፈጻጸሙ ዓይነት በቀላል ሁኔታ እንዲፈጸም የሚቀርብ ጥያቄ ነው፤*
2. *"ፍርድ" ማለት በወንጀል ጉዳይ በፍርድቤት የመጨረሻ ውሣኔ የተወሰነ ዋና ቅጣት፣ በተጨማሪ ቅጣት ወይም የጥንቃቄና የጥበቃ ውሣኔ ነው*

[119] የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት፣ ግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 74፣ አንቀጽ 28፡፡

[120] የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ መመሪያ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 25 ፣ አንቀጽ 9፡፡

[121] አቶ ገብረ መስቀል ደምለው፣ የአብክመ ይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት ባለሙያ፣ ስለይቅርታ አሰጣጥ የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ መጋቢት 2009 ዓ.ም.፡፡

[122] ስለፀረሽብርተኝነት የወጣ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 652/2001፣,*የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣* (2001)፣ አንቀጽ 31፡፡

[123] የፌዴራል ፍርድቤቶች አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 25/1988፣ *ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፡፡* (1988)፡፡ አንቀጽ 4(5)፡፡

መጠቀም[124]፣ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርና[125] ሌሎችም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚዳኙ የወንጀል አይነቶችን የሚመለከት ነው። ይኸውም እነዚህ ወንጀሎች በክልል ፍርድ ቤቶች የሚታዩት በውክልና ስልጣንና ይቅርታውም የሚሰጠው በፌዴራሉ መንግሥት ሆኖ ሳለ በአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ መመሪያ ላይ ይቅርታን የሚያስከለክሉ ወንጀሎች ተብለው መደንገጋቸው በሕግ ፊት ያለው ተቀባይነትና የመመሪያው ተፈጻሚነት ጉዳይ ነው።

ከወንጀሉ ባሕርይ ባሻገር የወንጀል ፈጻሚው ባሕርይ ለይቅርታ መስጠት ወይም መከልከላ እንደምክንያት ይወሰዳል። ወንጀል ፈጻሚው አደገኛ ባሕርይ ያለው ከሆነ ወንጀሎችን ደጋግሞ የመፈጸም ልምድ ያዳብራል ተብሎ ይገመታል። ደጋጋሚ ወንጀለኛ የሚለው ሐረግ ትርጉሙ ላይ መስማማት ባይደረስም በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 67 ስር የተመለከተውን ጽንሰሀሳብ ግምት ውስጥ በማስገባት ደጋግመው በወንጀል ጥፋተኛ የተባሉ ሰዎች ደጋጋሚነታቸው ለይቅርታ መከልከል እንደምክንያት ተደርጎ በመመሪያው ተመልክቷል።[126] በዚህ ድንጋጌ መሠረት ደጋጋሚ የሆነ ማንኛውም ወንጀለኛ የይቅርታ ተጠቃሚ መሆን አይችልም።ሆኖም በመመሪያው አንቀጽ 10፡-

> *ከዚህ በፊት በሰው መግደል ወንጀል ተፈርዶባቸው ከወጡ በኂላ ዳግመኛ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽመው የተፈረደባቸውን ሳይመለከት በማንኛውም ሕጋዊ የአፈታት ሥርዓት ከእስር ተፈተው አምስት አመትና ከዚያ በላይ በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀላቅለው የነበሩ የሕግ ታራሚዎች ዳግም ወንጀል ፈጽመው ቢመጡም የባሕርይ ለውጥ ማምጣታቸው በልዩ ክትትልና ግምገማ ከተረጋገጠና የይቅርታ አሰጣጥ መስፈርቱን አሟልተው ከተገኙ የይቅርታ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።*

የሚል ድንጋጌ አለ።

ይህ ድንጋጌ ደጋጋሚ ወንጀለኞችን የይቅርታ ተጠቃሚ የሚሆኑና የማይሆኑ ብሎ ለመለየት ያሰበ ይመስላል። በድንጋጌው ውስጥ "ከዚህ በፊት በሰው መግደል ወንጀል ተፈርዶባቸው ከወጡ በኂላ ዳግመኛ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽመው የተፈረደባቸውን ሳይመለከት" የሚለው ሐረግ ማንኛውንም አይነት የሰው መግደል ወንጀል በተደጋጋሚ ፈጽመው የተፈረደባቸው ታራሚዎች ምንም እንኳን በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 67 የተመለከተው አምስት አመት ካለፈ በኂላ የሰው መግደል ወንጀል የፈጸሙ ቢሆንም ደጋጋሚነታቸው ሳይሰረዝ እንዳለ ተቆጥሮ በዚሁ ምክንያት የይቅርታ ተጠቃሚ መሆን አይችሉም፤ የሚል መልዕክት ይሰጣል። ይህ የበለጠ ግልጽ የሚሆነው የድንጋጌው ሌላ ዘንግ በወንጀል ሕጉ የተመለከተው አምስት አመት ካለፈ በኂላ ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው በሰላም ሲኖሩ ሌላ ወንጀል ፈጽመው ወደማረሚያቤት ከመጡ ደጋጋሚነታቸው ሳይዘከር የይቅርታ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ መደንገጉን በሌላ መንገድ ሲታይ ነው። ምንም እንኳ ከፍ ብሎ የተመለከተው ብዥታ ወይም የሀሳብ ልዩነት በደጋጋሚነት ጽንሰሃሳብና ውጤቱ ላይ በጉልህ የሚንጸባረቅ ቢሆንም በደምሳሳው መረዳት የሚቻለው ደጋጋሚነት የወንጀለኞች አንዱ አደገኛ ባሕርይ በመሆኑ ይቅርታን

---

[124] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 4(10)።

[125] *ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርና ስደተኞችን በሕገወጥ መንገድ ድንበር መሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ*፣ አዋጅ ቁጥር 909/ 2007፣ *ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ*፣ (2007)፣ አንቀጽ 24 (1)።

[126] *የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ መመሪያ*፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 25፣ ቁጥር 10 እና የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ ግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 1፣ አንቀጽ 67።

ለማስከልከል በይቅርታ አሰጣጥ መመሪያው ላይ እንደምክንያት ሰፍሮ እየተተገበረ መሆኑን ነው፡፡

በመመሪያው ባይመለከትም ይቅርታን በተግባር እያስከለከለ ያለው የገንዘብ መቀጮ ነው፡፡ የይቅርታ ተጠቃሚ የሆነ አንድ ታራሚ በይቅርታ አሰጣጥ አዋጁና በመመሪያው የተመለከቱትን ቅድመሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ ቢያሟላም ከእስራት ቅጣቱ በተጨማሪ ወይም በሌላ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የገንዘብ ቅጣት ተወስኖበት ከሆነ ይህንን መቀጮ እስካልከፈለ ድረስ የይቅርታው ተጠቃሚ ሊሆን እንደማይችል ጥናቱ የተደረገበት ማረሚያቤት አሰራር ያሳያል፡፡ [127] በአጠቃላይ ይቅርታ በመርህ ደረጃ በኢፌዴሪ ሕገመንግሥትና በወንጀል ሕጉ የተመለከተውን ለማስፈጸም በወጡ የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅና መመሪያ የተመለከተቱትን መስፈርቶች አሟልቶ ለተገኘ ማንኛውም ታራሚ ሊደረግ የሚችል ቢሆንም ከላይ በቀረቡት ምክንያቶች የተነሳ ይቅርታው ሊነፈግ እንደሚችል ልብ ማለት ያሻል፡፡

## 5.5 ይቅርታ የሚሻርበት ሁኔታ

በቀደመው ርእስ እንደተገለጸው ይቅርታ በሕጉ የተመለከቱ ቅድመሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ የሚሰጥና ታራሚዎች የፍርድ ጊዜያቸውን ከመጨረሳቸው በፊት ከእስር የሚለቀቁበት መንገድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ መልኩ የተሰጠ ይቅርታ ሊሰረዝ የሚችልባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ይቅርታ የተደረገለት ሰው ይቅርታውን ያገኘው በሕገወጥ መንገድ ከሆነና ለሁኔታዎች ተገዥ ካልሆነ የተሰጠው ይቅርታ ሊሰረዝ ይችላል፡፡ ይቅርታው የሚሰረዝባቸው ሁኔታዎች በኢፌዴሪና በአማራ ክልል የይቅርታ አሰጣጥ አዋጆች እንደቅደምተከተላቸው በአንቀጽ 23 እና 15 እንዲሁም በአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ መስፈርት መወሰኛ መመሪያ አንቀጽ 13 ስር ተመልክተዋል፡፡ በዚህ መሠረት ይቅርታው በተጭበረበረ መንገድ የተገኘ ከሆነ፣ በቅድመሁኔታ ላይ የተመሰረተ ይቅርታ ከሆነ ቅድመሁኔታው ካልተከበረና ይቅርታ የተደረገለት ሰው ይቅርታ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ሦስት አመታት ውስጥ ሌላ አዲስ ወንጀል ፈጽሞ ጥፋተኛ ከተባለ የተሰጠው ይቅርታ ይሰረዛል፡፡[128]

ይቅርታው ይቅርታ ለተደረገለት ሰው ቢደርስም ባይደርስም በማጭበርበር ወይም በማታለል የተሰጠ ከሆነ ሊሰረዝ ይችላል፡፡ የይቅርታው መሰረዝ ውሳኔ የሚሰጠው በፌዴራል መንግሥት ደረጃ በሀገሪቱ ርዕሰብሄር ሲሆን በአማራ ብሄራዊ ክልል ደግሞ በክልሉ መስተዳደር ምክርቤት እንደሆነ በአዋጆቹ ተደንግጓል፡፡[129] ከዚህ ላይ ይቅርታን የመስጠትና የመሻሩ ስልጣን በክልል ደረጃ ከርዕሰመስተዳደሩ ይልቅ ለምን ለመስተዳደሩ ምክርቤት እንደተሰጠ በሕጉ አልተገለጸም፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት አቅራቢዎች እምነት የርዕሰመስተዳድሩ ሕገመንግስታዊ ስልጣን ከሀገሪቱ ርዕሰሄር ይልቅ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን ጋር የሚነጻጸር በመሆኑና ይቅርታ ደግሞ የአገሪቱ ሉአላዊነትና ህዝባዊነት መገለጫ (symbol of the nation) በመሆኑ

[127] ከባሕር ዳር ማረሚያቤት ባለሙያዎች፣ የስራ ኃላፊዎችና ታራሚዎች ጋር ስለይቅርታ አሰጣጥ የተደረገ የቡድን ውይይት፣ ግንቦት 2008 ዓ.ም.፡፡

[128] የፌዴራል የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ፣ ግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 23 አንቀጽ 23 እንዲሁም የአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ መመሪያ፣ ግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 25፣ ቁጥር 13(4)፡፡

[129] የፌዴራል የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ፣ ግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 23፣ አንቀጽ 23 (3 እና 4) እና የ አብክመ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ ፣ ግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 24፣ አንቀጽ 15(4)፡፡

እንደሆነ ያምናሉ፡፡ በአጠቃላይ ይቅርታ በብዙ መስፈርቶች ተመዝኖ እንደሚሰጥ ሁሉ ይቅርታው ከተሰጠ በኋላ ይቅርታ የተደረገለት ሰው ሊያከብራቸው የሚገቡ ቅድመሁኔታዎች ተላልፎ ከተገኘ በሕጉ በተመለከተው ስነሥርዓት መሠረት ሊሻርና ይቅርታ የተደረገለት ወንጀል ፈጻሚ ይቅርታውን ከማገኘቱ በፊት ወደነበረበት ሁኔታ እንዲመለስ ይደረጋል፡፡

## 6. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳብ

### *6.1 ማጠቃለያ*

በዚህ ጥናት የይቅርታ ጽንሰሃሳብ፣ አስፈላጊነትና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ከመዳሰሳቸውም በላይ በባሕር ዳር ማረሚያቤት የይቅርታ አፈጻጸም ምን እንደሚመስል ከኢፌዴሪ የወንጀል ሕግና ይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ እንዲሁም ከአብክመ ይቅርታ አሰጣጥ አዋጅና መመሪያ አንጻር ተቃኝቷል፡፡ በእነዚህ ሕግጋትና በይቅርታ አፈጻጸም ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችም ተለይተዋል፡፡ በዚህም መሠረት የይቅርታ አሰጣጥን አስመልክቶ የሚስተዋሉ የሕግና የአፈጻጸም ችግሮችንና መፍትሄዎቻቸውን በጥናቱ ውስጥ ለማካተት ተሞክሯል፡፡ የጥናቱ አንኳር ግኝቶችም እንደሚከተለው በአጭሩ ቀርበዋል፡፡

የክልሉ የይቅርታ አዋጅ የይቅርታን ዋና አላማ ሲያመላክት የታራሚዎችን ጥቅምና ፍላጎት ወደጎን በመተው በህዝብና በመንግሥት ጥቅም ላይ ብቻ ያተኮረ ሲመስል ይህም ከፌዴራሉ ተነጻጻሪ ሕግ ጋር ሲተያይ በይዘቱ የጠበበ ይመስላል፡፡ በተመሳሳይ የፌዴራሉም ሆነ የክልሉ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጆች የወንጀሉ ሰለባ የሆኑትን ግለሰቦች ፍላጎትና ጥቅም ግምት ውስጥ ባለማስገባታቸው የይቅርታ አላማ የህዝቡን፣ የመንግሥትንና የታራሚዎችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅሞች ማሳካት ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡

የይቅርታ ጥያቄ በታራሚው ባለቤት፣ በቅርብ ዘመድ ወይም በሌላ ሰው አማካኝነት ሲቀርብ ታራሚው ፈቃደኛ ስለመሆኑ በፊርማው እንዲያረጋግጥ የክልሉ አዋጅ በግልጽ አለመደንገጉ የታራሚው ፈቃድ ከግምት ውስጥ እንዳይገባ ያደርጋል፡፡ ይህም የይቅርታ ጥያቄው ከታራሚው እውቅና ውጭ ለይቅርታ አድራጊው አካል ቀርቦ ያለታራሚው ፈቃድና ዝግጅት ይቅርታው ሊሰጥ የሚችልበትን አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል፡፡

የይቅርታ ጥያቄ በመንግሥት አካላት በኩል ሲቀርብ ይኸው ጥያቄ በፌዴራል ለይቅርታ ቦርዱ ሲሆን በክልሉ ደግሞ ለክልሉ መስተዳደር ምክርቤት መቅረቡ ሂደቱን ከማርዘሙም በላይ የፖሊሲ ምክንያቱ ግልጽ አይደለም፡፡

ከመመሪያው በይቅርታ ሊቀነስ ወይም ሊሻሻል የሚችለው የቅጣት አይነት እስራት ብቻ እንደሆነ የሚያመላክቱ መስፈርቶችን ይዞ መውጣቱንና የይቅርታ ተጠቃሚ የሚሆኑትም የዚሁ ቅጣት ፍርደኞች ብቻ መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ይቅርታ በሁሉም የቅጣት አይነቶች ላይ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል በወንጀል ሕጉ ከተመለከተው ድንጋጌ አንጻር ሲታይ መመሪያው የይቅርታን ጽንሰሃሳብና አፈጻጸም ውስን እንዲሆን አድርጎታል፡፡

የክልሉ የይቅርታ አሰጣጥ መመሪያ እርቅ ለይቅርታ እንደቅድመሁኔታ በተመለከተባቸው የወንጀል አይነቶች ላይ በእርቁ ሊሳተፉ የሚገባቸውን የተጎጂ

የቅርብ ቤተሰቦችን በቅደምተከተል ሲያመላክት ይህ ቅደምተከተል እርቅን ለመፈጸም በልጆች መካከል ወይም በወላጆች መካከልና በሌሎቹም ቤተዘመዶች መካከል እንዴት ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል በግልጽ ባለመመልከቱ የእርቅን አፈጻጸም ወጥ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ እርቅ ለሰው መግደልና የመግደል ሙከራ ወንጀሎች ላይ ብቻ የይቅርታ መስፈርት ሆኖ መመልከቱ፣ ነገርግን በሌሎች መሰል ከባድ ወንጀሎች ላይ አለመጠየቁ እርቅ ለይቅርታ ያለውን ፋይዳ አጠያያቂ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

በመመሪያው ከ አስራ ሦስት አመት በታች ፍርደኛ ለሆኑ ነብሰጡር ሴቶች የይቅርታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ልዩ ስሌትን ሲያመላከት ከዚያ በላይ ለተፈረደባቸው ነብሰጡር ሴቶች ትኩረት አለመስጠቱ በመሰል ሴቶች መካከል ልዩነትን የሚፈጥር ይሆናል፡፡

የይቅርታ አሰጣጥ መመሪያው የባሕርይ መሻሻልን እንደቅድመሁኔታ ቢያመላከትም የባሕርይ መሻሻሉ ዝርዝር መለኪያ አለመዘጋጀቱ ለአፈጻጸም አስቸጋሪ ሆኗል፡፡

ይቅርታን የሚያስከለክሉ የወንጀል አይነቶች በመመሪያው የተለዩ ቢሆንም የፖሊሲ ምክንያታቸው ግልጽ አለመሆኑ ሌላው በመመሪያው የተስተዋለ ክፍተት ነው፡፡

በአፈጻጸም ረገድ ከይቅርታ አሰጣጥ ጋር ተያይዞ በባሕር ዳር ማረሚያቤት የሚስተዋሉ ችግሮች ደግሞ በይቅርታና የእርቅ አፈጻጸም ሂደት ውስጥ የሚሳተፉ አካላት መብዛትና ሂደቱም ረጅምና የተንዛዛ መሆኑ፣ አስታራቂ ሽማግሌዎች እርቁን በአግባቡ አለመፈጸማቸው፣ የይቅርታ ተጠቃሚዎች እርቅን ለመፈጸም ተበዳዮችንና ቤተሰቦቻቸውን በቅርበት በቀላሉ ማግኘት አለመቻላቸው፣ ለእርቅ የሚጠየቀው የገንዘብ ካሳ መጋነንና በአካባቢው ባህል ያልተለመደ መሆን፣ የይቅርታ ተጠቃሚዎቹ ለአስታራቂ ሽማግሌዎች አበልና የስራ ማስካሄጃ እንዲከፍሉ መገደዳቸውና የይቅርታ ተጠቃሚዎቹ ሌሎችን የይቅርታ መስፈርቶች ቢያሟሉም በፍርድቤት የተጣለባቸው የገንዘብ መቀጮ ካለ ይህንኑ እስካልፈጸሙ ድረስ የይቅርታ ተጠቃሚ አለመሆናቸው ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 6.2 የመፍትሄ ሐሳብ

ከፍ ብሎ የተመለከቱትን የሕግ ክፍተቶችና የአፈጻጸም ችግሮች መሠረት በማድረግ የመፍትሄ ሃሳቦች ከዚህ በታች ቀርበዋል፤

- በአብክመ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ ውስጥ የሰፈረው የይቅርታ አላማ በይዘት ጠበብ ያለ ስለሚመስል ከፌዴራሉ የይቅርታ አዋጅ ጋር እንዲጣጣም ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡
- በፌዴራሉም ይሁን በክልሉ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ ውስጥ የተለመከተው አጠቃላይ የይቅርታ አላማ የወንጀል ሰለባዎችን ፍላጎትና ጥቅም የማያስተናግድ በመሆኑ የክልሉ የይቅርታ አሰጣጥ አዋጅ ይህንን በሚያካትት መልኩ እንዲሻሻል ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡
- የይቅርታ ጥያቄ በታራሚው ባለቤት ወይም የቅርብ ዘመድ ሲቀርብ ታራሚው እንዲፈርምበት በማድረግና ጥያቄው በፍትህ ቢሮ ወይም በማረሚቤት ጽ/ቤት በኩል ሲቀርብ ጥያቄው ወደመስተዳደር ም/ቤት ከሚቀርብ ይልቅ ለቦርዱ እንዲቀርብ ለማድረግ ሕጉ ቢሻሻል፤

- በእርቅ ሂደት ውስጥ ባለቤት ሆነው መሳተፍ የሚገባቸው የተጎጅ ቤተሰቦች በግልጽና በማያሻማ መልኩ ከትርጓሜ ባለፈ ተለይተው በሕግ ቢመለከቱ፤
- የይቅርታ አሰጣጥ መመሪያው አስራ ሦስት አመት በታች እስራት የተቀጡ ነብሰጡር ሴቶች የእስራት ቅጣቱ በልዩ ስሌት ተሰልቶ የይቅርታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሲያመለክት ከ13 አመት በላይ የእስራት ቅጣት የተጣለባቸው ነብሰጡር ሴቶች ግን የዚህ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ መደረጉ አድሎን ስለሚፈጥር ቢስተካከል፤
- የባሕርይ መሻሻልን መለካት የሚያስችል ዝርዝር መለኪያ በይቅርታ አሰጣጥ መመሪያው እንዲካተት ቢደረግ፤
- ይቅርታ ከእስራት ባሻገር በወንጀል ሕጉ መንፈስ መሠረት ለሌሎች ቅጣት አይነቶችም ተግባራዊ የሚሆንበት አሰራር በመመሪያው እንዲካተት ቢደረግ፤
- እርቅ በግድያና በመግደል ሙከራው ወንጀል ላይ ለይቅርታ እንደሚያስፈልግ መመሪያው ስለሚጠይቅ መፈጸሙ ግድ ቢሆንም አፈጻጸሙ ለታራሚዎች አዳጋች ሆኗል፡፡ ይህም የሆነው በባለቤትነት እየተከታተለ የሚያስፈጽም አካል ባለመኖሩ ስለሆነ ይህን ተከታትሎ የሚያስፈጽም ባለሙያ በየወረዳው በሚገኙ በአስተዳደርና ጸጥታ ጽ/ቤቶች ቢመደብ፤
- እርቅን ለሚያስፈጽሙ ሽማግሌዎች ስልጠና ቢሰጥ፤ ክትትልና ድጋፍ ቢደረግ፤
- የግል ተበዳዮች ለመታረቅ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ከቀሩ እንዲሁም የተጋነነ ካሳ ሲጠይቁም ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ተቆጥሮ በመመሪያው መሠረት ማስረጃ ሲቀርብ የይቅርታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ቢደረግና ለበቀል እንዳይጋለጡ ተገቢ የክትትል ሥርዓት ቢኖር፤
- ከእስራት በተጨማሪ በገንዘብ መቀጮ የተቀጡ ታራሚዎች ገንዘቡን መክፈል አለመቻላቸው የይቅርታ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ከሚደረግ ይልቅ በሕጉ መሠረት የሚከፍሉበት ሁኔታ ቢመቻች ወይም ፍርድቤቱ ተለዋጭ ቅጣት የሚያመቻችበት ሥርዓት ቢዘረጋ፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የክፍያውን አፈፃፀም መሠረት በማድረግ ብቻ የወር ተከፋይ በሆኑን እና የወር ተከፋይ ባልሆኑት መካከል ምክንያታዊ ያልሆነ ልዩነት በመፍጠር የወር ተከፋይ ያልሆኑት ለበዓል ቀን ክፍያ እንደማይፈምላቸው በማድረግ ከወር ተከፋዮች ጋር በዕኩልነት የመታየት ህገ-መንግሥታዊ መብታቸውን የሚጥስ ይሆናል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ በሣምንት የዕረፍት ቀናት እና በህዝብ የበዓል ቀናት ክፍያ እንዲፈጸምላቸው በህጉ ላይ የተቀመጠበት ዋና ምክንያት ሠራተኛው ህይወቱን ተገቢ በሆነው መንገድ (decent life) እንዲመራ ለማስቻል ነው፡፡ መሠረታዊ ዓላማው ይህ ከሆነ ምክንያቱ ለወር ተከፋዩ ብቻ ሳይሆን በተመሳሳይ ሁኔታ ለቀን ተከፋዩም ተፈፃሚ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ ይህ ብቻም አይደለም፡፡ በሶሺዮ ኢኮኖሚክ ኮቬናንት በአንቀጽ 7 ላይ ሠራተኞች በበዓል ቀናትን ክፍያ የማግኘት መብት እንዳላቸው የተደነገገ እና ኢትዮጵያም የዚህ ኮቬናንት ፈራሚ አገር በመሆኗ በስምምነቱ ተገዳጅ ነች፡፡ ስለሆነም ህገ-መንግሥቱን፣ የአሠሪና ሠራተኛ ህጉን እና ኮቬናንቱን በማገናዘብ አስተሳስረን ስንመለከተው ህግ አውጪው ከዚህ ስሜት በመራቅ የወር ተከፋይ ያልሆኑ ሠራተኞች በስራ ውላቸው ወይም በህብረት ስምምነት ክፍያ እንዲፈጸምላቸው የሚፈቅድ ድንጋጌ ከሌለ በቀር ለበዓል ቀን ክፍያ አይፈጸምላቸውም ብሎ አቀዋም እንደወሰደ ማሰብ አይቻልም፡፡ እንዲያውም ድንጋጌው ብዙ ጊዜ ከሠራተኞቻቸው ጋር በድርድር የኅብረት ስምምነት ለመፈጸም የማይፈልጉ አሠሪዎችን የህብረት ስምምነት እንዲኖራቸው የሚያተጋ መሣሪያ ተድርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ ከዚህ ያለፈ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም፡፡ ስለሆነም የወር ተከፋይ ያልሆኑ ሠራተኞች ከአሠሪያቸው ጋር በሥራ ውል ወይም በህብረት ስምምነት የሚወስኑት ከፍ ሲል በተጠቀሱት ምክንያቶች የክፍያውን መጠን ብቻ ነው፡፡ በህብረት ስምምነት ወይም በሥራ ውል የተወሰነ የክፍያ መጠን ከሌለ ግን ማንኛውንም ሠራተኛ በቀን ስምንት ሰዓት እንደሚሰራ ታስቦ በመርህ ደረጃ የተጠበቀለትን ክፍያ የማግኘት መብት ተግባራዊ ሊሆንለት ይገባል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ለበዓል ቀናት ክፍያ ይገባቸዋል በማለት የሰጠው ፍርድ የሚነቀፍበት ምክንያት አላገኘንም፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ውሳኔ**

አመልካቾች ለሳምንት የዕረፍት እና ለበዓል ቀናትን ክፍያ ሊፈጸምላው ይገባል በማለት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሆነ ህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡

ኪሣራና ወጪ ይቻቻሉ፡፡

**ትዕዛዝ**

የባህር-ዳር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔው የጸና መሆኑን አውቆ በጸናው ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ግልባጩ ይተላለፍለት፡፡ ይጻፍ፡፡

የተሰጠ ዕግድ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡